# ይስሐቅ

## የኦሪት ዘፍጥረት 25-28 ታሪክ


### በኪቲ አና ግሪፊትስ

ሥዕል በዊሊ

ትርጉም፡- በኃይሌ ጀናይ

እርማት፡- ዮዲት ኃይሉ እና ዳንኤል ተሾመ

ዋና አርታኢ፡- ዘነበ ገብረሐና



BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

**የአሳታሚው መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።**

Copyright © 2006 by SIM Ethiopia, Addis Ababa. Originally published in English Under the title of ISAAC. copyright © Kitty Anna Griffiths, 1978 Bible Stories Alive. A division of A Visit With Mrs. G. Ministries Inc., 2851 St. Clair Ave. East, Toronto, Canada M4B 1N4

***1ኛ እትም 2000 ዓ.ም***

**1**st Edition 2008.

**አሳታሚ** } **የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ**
Publisher } SIM Publishing

**የፖ.ሣ.ቁጥር** } ***127 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ***
P.O.Box } Addis Ababa, Ethiopia

**ስልክ** } ***011-349-3252፣ 011-551-2973***
Tel.

**ኢ-ሜይል** } simmedia@ethionet.et
E-mail

**የኮምፒውተር ጽሑፍ:- ጥሩ ወርቅ በቀለ**
**የገጽ አቀማመጥ:-**

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

# በዚህ ተከታታይ መጽሐፍ እትም ውስጥ ቀደም ብለው የተዘጋጁ መጻሕፍት

# ታሪኮች


1. ድርብ ችግር! ....................................................5
2. ቄንጆ ወጥ! (ጣፋጭ ወጥ) ..........................17
3. «ድብድብ የለም!» (ፀብ የለም) ......................32
4. የውኃ ጉድጓድ! ጉድጓድ! ጉድጓድ ..................45
5. እነዚያ ምራቶች! ..............................................60
6. እናት የፈለገችውን አገኘች ................................72
7. ነገር ግን ያገኘችውንም አጣችው .....................87

ታስታውሳላችሁ ........................................................99

# 1

# ድርብ ችግር!

እነኛ መንትዬዎች ከመወለዳቸው በፊት እንኳ ይጣሉ ነበር ብልህ ታምናለህ? ምስኪኗ እናታቸው ርብቃ ተጨንቃ ነበር። ችግር ሲገጥማት ወደ ዶክተር ዘንድ ሮጥ ብላ ምሬቷን እንዳትናገር በዛን ጊዜ ዶክተር የሚባል ነገር አልነበረም።

መቼም ምሬቷን ለባሏ መናገሯ አይቀርም። ለሃያ ዓመት ያህል በባሏ አጉረምርማለች! ምናልባት አሁን ይስሐቅ ማጉ ረምረሟን ለምዶት ይሆናል።



የምትለውን ብቻ አዳምጡ፡- «ስማ ይስሐቅ፣ አገሬን ካራን ጥዬ ከመጣሁ ሃያ ዓመት ሆኖኛል። ካራን ከዚህ ብዙ ይርቃል። የምወዳቸውን ዘመዶቼንም ከወጣሁ ጀምሮ አይቻቸው አላውቅም። ሚስትህ እንድሆን ለእኔ የእግዚአብሔር ጥሪ እንደ ነበ ረ አስባለሁ። ይህንን ስል እንድታምነኝ እፈልጋለሁ፣ አሁንም ቢሆን የአንተው እንጂ በዓለም ላይ የሌላ የማንም ሰው ሚስት

አልሆንም፡፡ ነገር ግን ለእኔ የገባኝ፣ ይመስለኝም የነበረው በእግዚአብሔር የተመረጠ ሕዝብ እናት እንደምሆን ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን እነሆ ከሃያ

ዓመት በኋላም እንኳ ምንም ልጅ የለንም፡፡ ስመጣ በጣም ወጣት ነበርኩኝ፤ አሁን ግን እንደምታውቀው ዕድሜዬ እየገፋ ነው፡፡»

«አሁንም ቢሆን ገና ወጣትና ቈንጆ ነሽ፡፡ የእኔ ውድ ርብቃ» አለ ይስሐቅ፡፡

«አዎን አዎን፣ ግን-ግን-»

«አሁን፣ አሁንም! አትጨነቂ! የእግዚአብሔርን ጊዜ ጠብቂ እስቲ፡፡

የእኔ ውዲቷ እናት ልዕልት ሣራ እኔን ስትወልድ ዘጠና ዓመቷ ነበረ፡፡»

«እኔ ግን ዘጠና ዓመት እንድሆን አልሻም»

«ገና እኮ ሠለሣ አምስት አልሆነሽም ርብቃ የእኔ ማር፡፡ ብዙ ጊዜ አለሽ፡፡ እግዚአብሔር እንደ ሆነ አይቸኩልም፡፡ ቃሉን ደግሞ ያከብራል፡፡»

«ታዲያ ከሃያ ዓመት በኋላ እኔ- እኔ-እኔ- እንደምሆን አይገድህም?

«አሁን አ-አሁን ርብቃ እንባሽን አብሽው፤ በዚችው ዕለት መሥዋዕት በማቀርብበት ሰዓት ይህንን ጉዳይ አንሥቼ እግዚአብሔርን አነጋግረዋለሁ፡፡ ወንድ ልጅ እንዲሰጥሽ እማጸነዋለሁ፡፡»

ርብቃ ይስሐቅን ጉንጬ ላይ ሳም አደረገችውና እንባዋን አበስ አበስ አድርጋ ፈገግ አለች። ብዙም ሳትቆይ እንዲህ አለች፣ «ይስሐቅ፣ እግዚአብሔር ጸሎትህን ሰምቶአል በመጨ ረሻ ወንድ ልጅ ልናገኝ ነው!»

ነገር ግን፣ ጊዜያት አለፉ፤ ርብቃ ደግሞ ጥሩ ስሜት አልተሰማትም። ሰውነቷ የራሷ መስሎ አልተሰማትም። ቀደም ብዬ እንዳልኩት ወደ ዶክተሩ ዘንድ ሄዳ ስለ ሁኔታው ልትገልጽ አልቻለችም።፤ ዳሩ ግን ድሮ ከካራን ይዛት ላመጣቻ ት ታማኝ ተንከባካቢዋ ለዲቦራ ጉዳዩን አጫውታታለች። ዲቦራ ሕፃናትን በተመለከተ ብዙ ብታውቅም እንዲህ ዓይነቱ ነገር ግን ፈጽሞ ሰምታ አታውቅም።



ከዚህ በኋላ ርብቃ፣ ለራሷ «በመጀመሪያ ደረጃ ይስሐቅ እግዚአብሔርን ጠይቆታል፣ እስቲ እኔ ራሴ ደግሞ አሁን እግዚአብሔርን ልጠይቀው መሰለኝ» አለች።

«እግዚአብሔር ሆይ» አለች። «እንግዳ ነገር ይሰማኛ ል። አንተ ነገሩ እንደሚገባህ አውቃለሁ። ማንም የሚገባው አይመስልም ለአንተ ግን ልነግርህ እችላለሁ። በውስጤ ጦርነት የሚካሄድ ይመስላል።

ሰዎች- ዲቦራ እንኳ ሳትቀር እንዲህ በማለቴ ያበድኩ ይመስላቸዋል:: እግዚአብሔር ሆይ እኔ እንጃ፣ ፈርቻለሁ! በጣም ፈርቻለሁ» አለች::

የእግዚአብሔር ምላሽ እንዲህ ሲል ወደ እርሷ መጣ:- «ርብቃ ሆይ፣ አትፍሪ:: ስለ ሁኔታው እኔን መጠየቅሽ ደስ ብሎኛል:: እንግዲህ እነግርሻለሁ አዳምጪኝ::

«የምትወልጂው መንታ ልጆችን ነው:: መንታ ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ሁለት ሕዝቦችም ናቸው:: ጠቡንም አስቀድመው ጀምረውታል::»

«እግዚአብሔር ሆይ አንተን በመጠየቄ ደስ ብሎኛል:: ምን እንደ ሆነ ካወቅኩኝ ከአሁን በኋላ አልፈራም::»

«ግን እኮ ነገሩ የተወሳሰበ ነው፣» አላት እግዚአብሔር በመቀጠል፤ «ይህም የሆነበት ምክንያት ታላቅዬው ታናሹን ስለሚያገለግል ነው:: በሌላ አባባል ለአብርሃም የገባሁለት የተ ስፋ ቃል የሚፈጸመው በትንሹ አማካይነት ነው::» ታዲያ ጦርነቱ ባይቆምም ርብቃ ስለ ጉዳዩ መጨነበን አቁማ ነበር ማለት ይቻላልካካ በእርግጥም መንትዮቹ ተወለዱካካ

የትኛው የቱ እንደ ሆነ ማስታወስ በጣም አስፈላጊ ነበርን ምክንያቱም ታላቅነቱን መሠረት አድርጎ የሚደረግ ብዙ ነገር ነበረና ነውካካ ወይም በዚህ ሁኔታ ታናሹን ማወቅ ነበር አስፈላጊው ነገርካካ

ተንከባካቢዋ ዲቦራ ሁለቱን ወንዶች ልጆች ለመንከባከብ

ዝግጁ ነበረችካካ መጀመሪያ የተወለደው ዔሳው ነበርካካ አስገራሚስ ሕፃን! በቀይ ፀጉር የተሸፈነ ልክ በፀጉራዋ ኮት የተጠቀለለ ይመስል ነበር። እርሱ ወዲያውኑ ዔሳው ብለው ሰየሙት ትርጉሙም «የተሸፈነ» ማለት ነውካካ

ሁለት ደቂቃ ያህል እንኳ ሳይቆይ ያዕቆብ ተወለደካካ የወጣው የዔሳውን ተረከዝ ግጥም አድርጎ ይዞ ነበር። ስሙን ያዕቆብ አሉት። ትርጉሙ «ያዥ» ማለት ነው።

ተንከባካቢዋ ዲቦራ የሕፃናቱን ገላ በጨው አሽታ በመጠቅለያ ጨርቅ እየጠቀለለች ሳለች፣ አንዱ ልጅ የሌላውን ተረከዝ ይዞ መውጣቱ አንድ ትርጉም ይኖረዋል ብላ ነበር።



በታላቁ ሰፈር (ካምፕ) እንዴት ያለ ታላቅ መነጋገሪያ ሆኖ ነበር! ነገሩ የግድ ምልክት ነው ይሉ ነበር። የሆነ ትርጉም ነበ ረው። ትንሹ ታላቁን ይቀድመዋል፤ ምናልባትም ያዝዘዋል በሚለው ላይ ሁሉም ተስማሙ። እናታቸው ርብቃ፣ ስለ እነርሱ ከእግዚአብሔር የሰማችው መልእክት ነበራት፡- ይኸውም ታላቅየው መንታ ታናሹን መንታ ያገለግላል።

ያው በርግጥ፣ እግዚአብሔር እንደ ሁልጊዜው ምን እንደሚያደርግና እንዴት እንደሚያደርግ ያውቅ ነበር። ዳሩ ግን በዚህ ቤተሰብ ውስጥ እያንዳንዱ ግለሰብ እግዚአብሔርን ለመርዳት እርሱ በሚያደርገው ነገር ውስጥ ጣልቃ ገብቷል። ጣልቃ ባይገቡ ግን ሁሉም ነገር በትክክል ይካሄድ ነበር። አባት ጣልቃ ገባ፤ እናት ጣልቃ ገባች፤ ከመንትዬዎቹ ታላቁ፣ጣልቃ ገባ፤ ተናሹም ጣልቃ ገባ። ሁሉም በአንድ ላይ ትልቅ ምስቅልቅል ውስጥ ገቡ።

ምንም እንኳ እናት ታላቅ ሊሆን ያለው ትንሹ መንትያ እንደ ሆነ እግዚአብሔር የተናገረ መሆኑን ለአባትየው ብትነግ ረውም አባትየው ግን ልብ አላለም። ይህንን ሁሉ ልዩነት ያመጡት በመውለጃ ጊዜ የተከሰቱት እነዛ ሁለት ደቂቃዎች ናቸው። አባታቸውም ዔሳው ታላቅ እንደ ሆነ ደምድሟል፤ መቼስ አንዱ መንታ ቀድሞ መምጣት ነበረበት። ዔሳው ቀድሞ መጥቷል፤ስለዚህ ያለው ሁኔታ ይኼው ነው።

ዔሳው የይስሐቅ የበኵር ልጅ ነበር፣ ይስሐቅም የሚንከባከበው እንደዛው ነበር። ልክ በንጉሣዊ ቤተሰብ ታላቅየው ልጅ ተተኪ ንጉሥ እንደሚሆን ሁሉ በድሮ

ዘመንም ስሙንና ክብሩን የሚቀበለው የበኩር ልጅ ነበር። ስለዚህም በይስሐቅ አመለካከት (አመለካከቱም አግባብነት ያለው ነበር)፣ በኩር ልጅ ዔሳው ነበር።

የመንትዮቹ እናት የሆነችው ርብቃ እግዚአብሔር ያለውን ነገር ታውቅ ነበር እርሱም፣ እዚህ ላይ ለየት ባለ መልኩ በኩር የሆነው ትንሹ መንታ ያዕቆብ ነበር። ነገሩን በእግዚአብሔር እጅ ከመተው ይልቅ ወደ ያዕቆብ አደላች። እንደምታውቁት፣ ቤተሰብ በሁለት ጐራ ተከፍለው ተፎካካሪ ቡድኖች ሁኑ። አንደኛው ጐራ የይስሐቅን መሪነት የያዘ የዔሳው ሲሆን ሌላው ደግሞ የርብቃ መሪነት የያዘ የያዕቆብ ቡድን ነበር።

እንዲህ ያለ ነገር፣ በስፖርትና በጨዋታ ጊዜ ጥሩ መዝናኛ ሊሆን ይችላል በቤተሰብ መሃል ሲከሰት ግን መከራ ይሆናል!

ምንም እንኳ መንትዮቹ በመጠንና በቅርጽ ተመሳሳይ እኩል ቢሆኑም፣ ተፈጥሮአቸው ግን ፍጹም የተለያየ ነበር።

ዔሳው ፍልቅልቅ፣ ግድ የሌለው፣ ረባሽ እና ሳቂታ ልጅ ነበር። ቍጡ ስለነበር፤ ሲናደድ ይጮሃል ነገር ግን ቶሎ ይበርድ ነበር። ደግሞም አኩራፊ አልነበረም።

እርሱ ደፋርና ጀግና ነበር- እጆቹን በግብርና ላይ ለማዋል ደስ ይለዋል። አባቱ ከጓደኞቹ ጋር እየሄደ እንዲያድን ይፈቅድለት ነበር። ስለዚህ ዔሳው በጣም ጉበዝ ተኳሽ ሆነ። አደን ይወድ ነበር።



ጨዋታዎችን መጫወት ተለማመደ:: ይሁን እንጂ ምግብ ለማብሰል ደንታ አልነበረውም:: ነገር ግን፣ በአደን ገድሎ ያመጣቸውን የዱር ፍየሎችን ከሽኖ ጣፋጭ  ምግብ ማድ ረግ ተምሯል:: አባቱ ይስሐቅ ደግሞ ያንን ጣፋጭ ምግብ ይወድደው ነበር::

ይስሐቅ ቁጭ ብሎ ሲመገብ፣ ዔሳው ደግሞ ስለአደኑ በዝርዝር ያጫውተው ነበር፡፤ ምናልባት አደኑ ሁለት ወይም ሦስት ቀን ፈጅቶበት ይሆናል:: ሽማግሌው ይስሐቅ ምግቡን እየተመገበ በአሳቡ ቋጥኙን ሲወጣ፣ አድብቶ ሲያድን፣ ወንዞችን ሲዘል፤ ልብሱ ሲቀደድ፣ እጆቹና እግሮቹ ሲቦነጫጨሩ፣ ነፋሱ ፊቱን ሲገርፈው፣ ዝናቡ ልብሱን ሲያበሰብሰው ይመለከታል:: በእርግጥ ይስሐቅ ሥጋውን ከአጥንቱ እየነጨ በአደን ስሜት ውስጥ ነበር::

ይስሐቅ ራሱ ቢያድን እንዴት በወደደ ነበር! ዳሩ ግን ዓይኖቹ ደክመዋል፡፡ ደካሞች ነበሩ- ከቅርብ እንጂ ከሩቅ ለማየት አይችልም፡፡ ዓይነ ስውር ለመሆን ምን ቀረው ብላችሁ ነው፡፡ በቀስት አድኖ መግደል ይቅርና ወደ አደን ስፍራ እንኳን በደህና መመላለስ አይችልም ነበር፡፡

ወደ አደን እንኳንስ በቀስት ሊወረውር ይቅርና በደህና መመላለስ አይችልም ነበር!

ይስሐቅና ልጁ ዔሳው ጓደኞሞች ነበሩ፡፡ አንድ ላይ ሆነው እንዴት ይስቁና ይጫወቱ ነበር! ያዕቆብ፣ «አባዬን እኔ ሳናግ ረው የተለየ ይናል፡፡ ብሎ ለእናቱ ለርብቃ አጉረመረመ፡፡ «ከእኔ ጋር አይስቅም፡፡ የምንወያየው ስለ ሥራ ብቻ ነው- መንጋዎቹና በውኃ ጉድጓዶቹ ላይ ስለሚነሡ ጭቅጭቆች፡፡ ስለ አንዳንድ ቁም ነገሮች በማሰቤ ደስ እንደሚለው አምናለሁ፡፡ ሆኖም ግን ከእኔ ጋር አይስቅም አይቀልድምም፡፡ በአጠቃላይ እኔን ብዙም የሚወደኝ አይመስለኝም፡፡»

«አትጨነቅ የእኔ ልጅ፡፡ አንተ የእኔ ልጅ ነህ» አለች ርብቃ፡፡

ያዕቆብ በአሥራ ስድስት ዓመቱ የተከናወነለት እረኛና በግ ጠባቂ ነበር፡፡ የእንስሳቱን በረት በደንብ አድርጎ ይዞታል፡፡ አባቱ ይስሐቅ በጣም ሀብታም ሰው ነበር፡፡ ራሱ ካከማቸው ሀብት ሌላ የአባቱን የአብርሃምን ሀብት ሁሉ ወርሶ ነበር፡፡

«እኔ ታላቅ ብሆን ኖሮኮ እማዬ አባቴ ከእኔ ጋር ይጫወትና ይስቅ ነበር፤ ልዩ ወዳጄም ይሆን ነበር» አለ ያዕ ቆብ፡፡

«በል አሁን መጨነቅህን አቁም ያዕቆብ፣ አንተ የእኔ ልዩ ወዳጄ ነህ። ከእኔ ጋር በቤት ስትሆን ደስ ይለኛል።»



«አደን ብወድ እመኛለሁ ነገር ግን ለብዙ ቀናት በበረኻ ላይ መዞሩ፣ መራቡና እንቅልፍ ማጣቱ ያስጠላኛል። እንደዚህም ሆኖ አንዳንድ ጊዜ አንድም የሚታዩን ይጠፋል። አባዬ ግን፣ ስለዚህም ቢሆን መስማት ደስ ይለዋል ዔሳውን በሚያዳምጥበት ጊዜ ደስ ይለዋል፣ ይደነቃል። ዓይኖቹ ያበራሉ፣ እላለሁ ግን በጣም ደካማ ናቸው፤ ምስኪን አባዬ!

«በተቻለኝ መጠን ስለ ከብቶቹና ስለ በጎቹ ብነግረውም አይደነቅም። የምንነጋገረው ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያወጡ ብቻ ነው። ይህም ቢሆን እምብዛም አይማርከውም- ፍጹም አይደነቅበትም። ከመጠን በላይ ገንዘብ ስላለው ነው መሰለኝ ደንታ የሌለው።»

«ያዕቆብ ያንተን እርዳታ እርሱ ዋጋ እንደሚሰጠው ልነግርህ እፈልጋለሁ። ከብቶቹንና በጎቹን የያዝካቸው ጥሩ አድርገህ ነው። አባትህም እንደሚያመሰግንህ አውቃለሁኝ።

ደግሞም አንድ ቀን የነገዱን መሪነት ለአንተ እንደሚሰጥህ አትርሳ:: ለዔሳው ሳይሆን ለአንተ፤ ለአንተ ይሰጥሃል::

«ዔሳው እንደ ሆነ ባለፈው ዓመት በአያትህ ቀብር ላይ እንዳየኸው እንደ አጐትህ እስማኤል አይነት ነው:: እርሱና አባትህ የአያትህን የአብርሃምን አስከሬን ማክፌላ በሚገኘው የመጨረሻው ማረፊያ ዋሻው ወስደው በልዕልት ሣራ አጠገብ ሲያኖሩት አይተሃል:: የመጨረሻ አክብሮታቸውን ለመግለጽ በዚያን ቀን የመጣው ሕዝብ አቤት ብዛቱ::

በዚያ ቀን ለእርሱ የነበረው አክብሮት ለመጨረሻ ጊዜ ሊገልጽለት የመጣ ሕዝብ አቤት ብዛቱ!



«አያትህ አብርሃም እንዴት ያለ ድንቅ ሰው ነበር መሰለህ! ገና ሚጢጢ ልጅ ሳለህ በእግዚአብሔር የተመረጥክ መሆንህን

ስለሚያውቅ ይንከባከብህ ነበር። «የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ» ይል ነበረ። ግሩም የሆነ አያት አጣህ አይደል እንዴ?

«በእርግጥ አጎትህ እስማኤል የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመራ ሰው አልነበረም። ልክ እንደዛው ዔሳውም አይሆንም። ስለዚህ አንተ መሆንህ ግልጽ ነው።»

«አዎን እማዬ፣ ነገር ግን እኔ ለመሆኔ አባዬን እንዴት ልንገልጽለት እንችላለን? ጊዜው ሲደርስ፣ በረከቱን ለዔሳው ይሰጠዋል፤ ከዚያ ደግሞ ነገሩ የመሸበት ይሆናል። አንዴ ከተ ሰጠ በረከቱ ላይመለስ ከእኔ አመለጠ ማለት ነው።»

«አይ፣ ብዙም አይቆይም ያዕቆብ። እስከዚያም ቢሆን እኔ አውቃለሁ። አንተም ብትሆን በእግዚአብሔር የተመረጥከው አንተ መሆንህን ታውቃለህ። ይህንን ታላቅ ነገድ ለመምራት በእግዚአብሔር የተመረጥከው አንተው ነህ።»



«ሰዎች ብኵርናቸውን መሸጥ ይችላሉ አይደል እማዬ? - ለሀብትም ሆነ ለሌላ ያላቸውን መብት ማለቴ ነው።»

«እንዴታ፣ በደንብ ይችላሉ እንጂ ያዕቆብ።»

«ነገር ግን እኔ የምገዛበት ምንም ነገር የለኝም። አንድ ቀን ግን ይኖረኛል፣ ይኖረኛል።

# 2

# ቄንጆ ወጥ! (ጣፋጭ ወጥ)

«ምን እየፈለግህ ነው ያዕቆብ?» በማት ርብቃ ከሽመናዋ ብቅ ብላ ከትልቁ የጥቁር ፍየል ፀጉር ከተሠራው ድንኳን ውስጥ ያለውን የምግብ ማከማቻ ሲያመሰቃቅል ያየችውን ታናሹን መንታ ልጇን ጠየቀችው። በቤርሳቤህ ሜዳ ላይ ተተ ክሎ የነበረው ድንኳን አንድ ጊዜ የርብቃ አማት የሆነችው የልዕልት ሣራ ነበረ።



«ምን እየፈለግህ ነው? ያዕቆብ?» ብላ ርብቃ፤ የሽመና ሥራዋን አቆመች።

«እንዴ እማዬ፣ ቅመሙ አልቋል እንዴ? እኔ የምሠራበት ያ ልዩ ቅመም? ያ የምሥር ወጥ ስሰራ የምጠቀምበት ቅመም ታውቂው የለ?» «ኧረ ፍጹም። ግንኮ ጨርሰን ሊሆን

ይችላል፡፡ ከገቢያ ከመንገዛው ዕቃ ዝርዝር ውስጥ ጨምረው፡፡ ጠዋት አንድ ሰው ወደ ቤርሳቤህ ይሄዳል፡፡ ግቢያችን ከገበያው አጠገብ መሆኑ እንዴት ጥሩ ነገር ነው፡፡ ለዚህም ነው እዚህ ከከተማው ውጭ ድንኳናችንን የተከልነው፡፡ አንድ ሰው ነገ ሽምቶ ያመጣልናል ያንተንም ቅመም ዝርዝሩ ውስጥ አስገባው፡፡ ለምንድን ነው ግን ያዕቆብዬ፣ የምሥር ወጥ ልትሠራ ነው እንዴ? ካለቅመም ሥራው? ለማንኛውም የምትፈልገው ትንሽ ነው፡፡

«እናቴ ካለቅመም ብሠራው ወጡ እንደማይጣፍጥ እኔም አንቺም ጠንቅቀን እናውቀዋለን?

አይሆንም! ዛሬ ልዩ የሆነውን የምሥር ወጤን ልሠራ ስለወሰንኩ ካንቺ አጠገብ መሆን እፈልጋለሁ፡፡ ዛሬ ከብቶቹና በጎቹ አካባቢ ምንም ችግር የለም፡፡ አገልጋዮቹ ይጠብቋቸዋል፡፡ እኔ ወጤን እሠራለሁ፡፡ የቤተሰቡ ምግብ ዛሬ እኔ ብሠራው አትደሰችም እማዬ?»

«መልካም ያቆብዬ» - አለችና እናቱ አንድ አሳብ መጣላት - «አንድ አፍታ ሄደህ አሮጊቷን ተንከባካቢ ዲቦራን ለምን አታናግራትም? ትንሽ ልጅ እያለህ ምግብ አበሳሰል ያስተማረችህ እርሷ ነበረች፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የምሥር ወጥ ልዩ አድርገህ መሥራት ያስተማረችህ እርሷ መሆኗ ጥርጥር የለውም፡፡ የምትፈልገው ቅመም ሳይኖራት አይቀርም፡፡ በዓለም ላይ ያሉት ቅመማ ቅመሞች ሁሉ አሏት፡፡ የምትወድደው ትንሹ ያቆብ መጥቶ ሲጠይቃት ደግሞ ደስ ይላታል፡» ልጅ ሳለህ በጣም ትንከባከብህ ነበር፤ አሁንም

ቢሆን እንደዚያው ናት። ወንድምህን ዔሣውንም እንዲሁ ትወደዋለች። ይሁን እንጂ ሁልጊዜ ለአንተ የምታደላ ይመስለኛል።»

ስለዚህ ያዕቆብ አሮጊቷ ነርስ ዲቦራ ወዳለችበት ድንኳን ሄደ። (እነርሱ የሚጠሯት «አሮጊቷ ተንከባካቢ ዲቦራ» እያለ ወይም ደግሞ «አሮጊቷ ዲቦራ» እያሉ ነበር። ይሁን እንጂ እርሷ በጣም አሮጊት አልነበረችም። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ከርብቃ የምትበልጠው ትንሽ ነው።) ዲቦራ በዘወትር ሥራዋ ላይ ተጠምዳ ነበር።

«ሰላም ዲቦራ! የምሥር ወጡ ቅመም ይኖርሻል? ሁልጊዜ አሠራሩን ስታሳይኝ ምሥር ወጥ ያለ ቅመም ጥሩ አይደለም ትይ ነበር። እናቴ አልቀባታል ። አንቺ በእርግጥ እንደሚኖርሽ ነግራኛለች። በዓለም ያሉ ቅመማ ቅመሞች ሁሉ አንቺ አሉሽ!»



«ወይ ጉድ! እስከ ዛሬ ድረስ ያ ነገር እየሠራ ነው?»

«አዎን:: አሁንስ እያስጠላሽ መጣ እንዴ ዲቦራ? አሠራሩን በምታሳይኝ ጊዜ ትወጂው ነበር::»

«የማልወደው እርሱን አይደለም! እርሱ ሲሠራ ሽታው ግቢውን ሁሉ ያስርባል:: ሽታው በሸተተኝ ጊዜ ቀኑን ሙሉ ስቆነጥረው እውላለሁ::»

ዲቦራ ያሏትን ቅመማ ቅመሞች መፈታተሽ ጀመረች:: «አሃ፣ አዎን አዎን» አለች «እስቲ እስቲ. . . አዎ፣ ይኸውና፤ እርሱ አይደለም እንዴ? ይህንን ነው አይደል የፈለግኸው?»

ያዕቆብ ቅመሙን አሸተተው:: ዲቦራ በጣም አመሰግናለሁ:: በትክክል እርሱ ነው::» ብሎ ያዕቆብ ወደ ድንኳኑ በራፍ አመራ::

«ዛሬ በጠዋት ወደ ወጥ ሥራ ልትገባ ነው ያዕቆብ:: ከአሮጊቷ ተንከባካቢህ ጋር ቁጭ ብለህ ለመጫወት አንድ ደቂቃ እንኳ የለህም? ድሮ በልጅነትህ እኮ ችግር ሲያጋጥምህ፣ ጉልበትህ ሲላጥ ወደ እኔ ሮጠህ መምጣት ደስ ይልህ ነበር:: ዔሣውም እንደዚሁ:: የምታስገርሙ መንትዮች ነበራችሁ::

«ዔሳው አልፎ አልፎ ይጠይቀኛል፤ በአደን ከገደላቸው እንስሳት ሥጋም ይዞልኝ ይመጣል:: «ይህችን ዳክዬ እስቲ ስሪልኝ ዲቦራ» ብሎኝ አንዲት ዳክዬ ከወለሉ አስቀምጦ ይሄዳል:: ወይም ደግሞ «ዛሬ ትልቅ ግዳይ ነው ዲቦራ» ይልና የበረኸ ፍየል ወለሉ ላይ ጥሎ ይሄድና ሠርታለች ብሎ በሚያስብበት ጊዜ ተመልሶ ይመጣል::



«ወንድምህ ትንሽ ትዕግሥት እንደሌለው ታውቃለህ:: ለራሱ የሚሆን ምግብ ለመሥራት እንኳ ትዕግሥት የለውም:: ነገር ግን ማንኛውንም ነገር እኛ እናደርግለታለን:: እርሱ ተወዳጅ ጓደኛ ነው:: ደግሞም ደንበኛ ወንድ ነው:: ምግቡን ማብሰል በተመለከተ ደካማ-በጣም ትዕግሥት የሌለው ነው:: ዳሩ እኛ ስለምንወደው ወደ ድንኳናችን ውስጥ ገብቶ እንዲገባ ወይም በውጭ ሆኖ ስለምንመግበው እርሱ ምን አስጨነቀው?»

«አባቱን ማጫወት እንደሆነ ያውቅበታል» አለ ያዕቆብ::

«እህ እርሱማ አዎ፤ ነገር ግን ያ ለአባት ብቻ ነው:: ይህም በአባቱ ዙሪያ እንዲሆን አጋጣሚ ዕድል ሰጥቶታል::

ዔሳው በአባቱ ከብዙ ነገር ያመልጣል። ቢገድል ያመልጣል ከአባቱ ጋር ሆኖ።

«በእነዚህ ቀናት ውስጥ ዔሳው ሚስት ያገኛል።» አለች ዲቦራ በመቀጠልም» እርሷም ምግቡን ታበስልለታለች። ኤ ሳው ሲመጣ የአካባቢው ሴቶች ሁሉ ያደንቁታል። እያንዳንዷ ሴት ይመርጠኛል ብላ ተስፋ ታደርጋለች።»

«ነገር ግን ዲቦራ፣ እዚህ አካባቢ ያሉት ሴቶች ሁሉ እኮ አሕዛብ ናቸው። አምላካችንን አይወድዱም፤ አንዳቸውም እንኳ። ከነርሱ መካከል በእርግጥ ማንንም አያገባም» አለ ያዕ ቆብ።

«አየህ» አለች ዲቦራ፤ «ዔሳው እንደ ሆነ ይህንን አያይም። እግዚአብሔርን የማታውቅ ሴት ማግባት ስሕተት እንደ ሆነ ደግመህ ደጋግመህ ብታስረዳውም ያንኑ ያደርጋል ፈጽሞ አይሰማም። ዔሳው የሚረዳው የሚያየውን ብቻ ነው። አሳቦች ለዔሳው መልካም አይደሉም። «የምፈልገውን ነገር በፈለግሁት ጊዜ እፈልጋለሁ፣ ይኸውም አሁን ነው።» ይላል።

ያዕቆብ በድጋሚ ለመሄድ ተዘጋጀ። ንግግሩ ዔሳው፣ ዔሳው፣ ዔሳው፣ ብቻ እንደሆነ አሰበ።

«ስለ ቅመሙ አመሰግንሻለሁ ዲቦራ፣» አላት በድንኳኑ በር እየወጣ ።

«በመምጣትህ ደስ ብሎኛል ያዕቆብ። አሮጊቷ ሞግዚትህን እንዳትረሳት! ሌላ ጊዜ ደግሞ መጥተህ ጠይቀኝ። ዔሳው እንደ ሆነ አደን ሄዶአል መሰለኝ። እኔና እናትህ ለአዲሱ የአደን ልብስ ልንለካው ፈልገን ልናገኘው አልቻልንም። ባለፈው ጊዜ

«ለዔሳው ልብስ የምንሰፋለት ጊዜ ደርሷል፤ ቆዳው ተ ዘጋጅቶአል፤ ዔሳው ግን የት አለ?» ብላ ነበር። አንተ እንደ ሆነ ይህንን ዓይነት ልብ አትለብስም። ላንተ የሚስማማው ጨርቅ ነው። የአንተን ልብሶች በቀላሉ በጥሩ ሁኔታ እንሠራልሃለን።

«ዲቦራ እንግዲህ በድጋሚ ስለ ቅመሙ አመሰግንሻለሁ። በቅርብ ወጤ መቅመሻሽን አዘጋጂ።

ስለዚህ ያዕቆብ ወጡን ለመሥራት ወደ እናቱ ድንኳን ተ መለሰ። መጽሐፍ ቅዱስ ወጡን «ቀይ ወጥ» ይለዋል። ነገር ግን አንድ የማውቀው ትንሽ ልጅ ትንሽ ለወጥ አድርጎ» « የድስት ሳልሳ» ብሎ ጠርቶታል። ይህም የተሻለ አጠራር እንደ ሆነ አስባለሁ።

«ለትንሽ ቅጠላ ቅጠል ስትል ረዥም ጊዜ ወሰድክ እኮ ያዕ ቆብ» አለችው ርብቃ።



እስከ አሁን ድረስ እየሸመነች ነበር።

«ቅመም ነው ኮ እማዬ»

«ይሁን እንጂ ጊዜ ወሰዶብሃል» አለችው መወርወሪያዋን በክሮቹ መሃል እያሾለከች።

«እንዴ እውነትም የአሮጊቷን ነርስ የዲቦራን

ልፍለፋ ሳዳምጥ ጊዜዬን አባክኜ የለምን እንዴ? እርሷ እንደ ሆነ ደኅና ለፈላፊ ነች፡፡ ትለፈልፋለች ትለፈልፋለች፤ አትለቅም፡፡ ብዙ የምታስበው ስለ ዔሳው አይደለም እንዴ? እማዬ በዓለም ላይ ያለው ዔሳው ብቻ እኮ ነው የሚመስላት» አለ፡፡ ያዕቆብ በሸክላ ድስት ባለው ውኃ ውስጥ ቀይ ምሥሩን እየጨመረ፡፡

«አዎን፣ ውዴ ያዕቆብ፣ ብዙ ሰዎች እንደዚ ናቸው፡፡ የእርሱን ተጫዋችነት ይወዱለታል» አለችው ርብቃ፡፡

«ሰዎች እኔን በጣም አይወድዱኝም፣ እማዬ፡፡»

«ምናልባት አንተ ዝምተኛ ስለሆንክ ምን እንደምታስብ እርግጠኞች አይደሉም፡፡ ምቾት አይሰማቸውም፣ አይቀላቸውም፣ ደግሞም ይጠራጠሩሃል፡፡ ጮሌና ተንኮለኛ ይሉሃል፡፡ አዎ ልጄን በተሳሳተ ሁኔታ ፈርጀውሃል፤ ሊረዱህ አልቻሉም፡፡ ይሁን እንጂ አትጨነቅ፡፡ አንተ በእግዚአብሔር የተመረጥክ ደግም የእናትህ ልጅ ነህ፡፡ እንደ አባትህ አርቆ አሳቢ፣ ረጋ ያልክና ቻይ ነህ፡፡ አባትህ ይስሐቅ በጣም ትዕግሥተኛ ነው፡፡»

«ግንኮ እማዬ፣ አባዬ የሚወደው ዔሳውን ነው፡፡ ዔሳው ለእርሱ ልዩ ነው፡፡ የፈለግሺውን ብትዪ ምርቃቱን እንደ ሆነ የበኵር ለእኔ ይሰጠኛል ብለሽ መገመት አትችይም፡፡

«ለምንድን ነው ወደዚህ ንትርክ ውስጥ የምንገባው? አራታችን ብቻ ሆነን ሳለ፣ አባዬና ዔሳው አንድ ላይ፣ እኔና አንቺ ደግሞ አንድ ላይ ሆነን እንነታረካለን፡፡ ለምንድን ነው

ግን እንዲህ የሆነው? ማቆም አንችልም?

ያዕቆብ ቅጠሉን፣ ቅመሙን፣ ነጭ ሽንኩርቱን እየጨመ ረ ወጡን ያማስል ነበር:: ልታሸትቱት ትችላላችሁ!



«ደግ ነው ያዕቆብ፤ እኔ እንጃ ስለዚህ ጉዳይ አስቤውም አላውቅ:: አየህ፣ አባትህ እኔን በዕድሜ በጣም ይበልጠኛል፤ በዚህ ዙሪያ መተፋፈር አለ፤ «መታፈር በከንፈር» ወይም ፈ ረንጆች «የተኛ ውሻ አትቀስቅስ» እንደሚሉት ዓይነት አስተ ሳሰብ አለ:: ለተረጋጋ ሕይወት ስትል ማንኛውንም ዋጋ ክፈል ለማለት ነው መሰለኝ:: አባትህ በሕይወቱ ምንም ፀብ አያውቅም:: አያትህ አብርሃም ባለጸጋ፣ ታዋቂ እና ተሰሚ ሰው ነበር:: አባትህ ያደረገው ነገር ቢኖር እርሱን መተካት

ብቻ ነበር፡፡ የአያትህ የነበረው ነገር ሁሉ የእርሱ ሆነ፡፡ ተቀናቃኝ የሆኑት አጐትህ እስማኤልና የኬጡራ ልጆች በስጦታ ረክተው ሩቅ አገር ይኖራሉ፡፡ አባትህን እንዳያስቸግሩት በማሰብ አያትህ አብርሃም ብዙ ስጦታዎች አሸክሟቸው ነበር፡፡

«ስለዚህ አባትህ በምንም ለምንም ብሎ አልለፋም አልተጣላምም፡፡ መቼም ግሩም የሆነ ተፈጥሮ ነው ያለው፣ ስለዚህ በጣም እወድደዋለሁ፡፡ አንተም በብዙ መንገድ እንደ እርሱ ስለሆንክ እወድድሃለሁ ያዕቆብ፡፡ አንተ የእኔ ምርጥ የሆንክ ልጅ ነህ፡፡»

«ልክ ነው፣ ነገር ግን እማዬ በቤተሰባችን አድሎ መኖሩ ጥሩ አይደለም፡፡»

«እሺ ያዕቆብ እንዲህ አስቀምጠው፡- የራሱን ጉዶሎነት አባትህ ያደንቀዋል፡፡ ዔሳው ያድናል፡፡ (በእርግጥ አባትህ ደግሞ የእርሱን ጣፋጭ የአደን ሥጋ ደስ ብሎት ይበላለታል፡፡) አዎን ዔሳው ያድናል፤ አባትህ ደግሞ ያንን ይወዳል- ጫካ መሄዱ፣ መታገሉ፣ ማድባቱ እና የዱር እንስሳን አባርሮ መግደሉ ደስ ይለዋል፡፡ ጨካኝ ከሆኑት አውሬዎች ጋር መጋፈጡ አባትህን በጣም ያስደነግጠዋል፤ ይሁን እንጂ ዔሳው ስለዚሁ ሁሉ ሲያጫውተው ደስ ይለዋል፡፡ አሁን ዓይኑ በደንብ ባለማየቱ አስቸግሮታል፤ ቢሆንም አባትህ በሕይወቱ አንድም ነገር ማደኑን አላውቅም፡፡ ከዚህ በብዙ ኪሎ ሜትሮች ርቄ ብኖርም እርሱ ለእኔ ሲል እንኳ አድኖ አያውቅም፡፡ ግን ያ ሌላ ታሪክ ነው፡፡

«ዳሩ ግን ያዕቆብ፣ ወደ ማበላለጡ ጉዳይ እንመለስና አባትህ ዔሳውን አብልጦ ይወድደዋል። ነገሮቹን ሚዛናዊ ለማድረግ ደግሞ እኔ አንተን አብልጬ እወድሃለሁ! ይኸው ነው፤ ሌላ ምንም ነገር የለውም።»

« ያ ባርኮት የምትዪውን ግን እማዬ ከአባቴ ለመቀበል ፈጽሞ የማይቻል ነገር ነው።»

«ምንም እርግጠኛነት የለም ነገር አይደለም ያዕቆብ። ከመወለድህ በፊት እንደምታገኘው እግዚአብሔር ነግሮኛል።»

ያዕቆብ ድስቱን ከፊት አደረገና ወጡን አማሰለው። ከወጡ ውስጥ የነጭ ሽንኩርቱ ሽታ ያውዳል።



«አቤት ሽታው እንዴት ግሩም ነው ያዕቆብ! እውነትም አንተ ወጥ መሥራት ትችልበታለህ!»

«አንቺም እኮ ጥሩ ትሠሪያለሽ እናቴ። አሁን

እንደተናገርሽው አባቴ አድኖ ሊያመጣልሽ አያስፈልገውም ነበር፡፡ ምን ማለትሽ ነበር?» ሲል ያዕቆብ ጠየቃት አሁንም በድጋሚ ወጡን ለማማሰል ድስቱን ከፈት አድርጎ፡፡ «አደን ሄዶ እንስሳን ሊያመጣልሽ አላስፈለገውም ስትዪኝ ምን ማለትሽ ነበር?»

«አይ ያዕቆብ» አለች ርብቃ፤ ዓይኖቿም በሩና «የአያትህ አሽከሮች ለእኔ ለማደን ካራን ይመጡ ነበር፡፡»

«አሽከሮቹ?»

«አዎን ኤሊዔዘር፡፡ ያ ቸርና የዋሁ ኤሊዔዘር፡፡»

«እንዴት ብሎ?»

«መልካም፣ አያትህ ባከባቢው የነበሩ ልጃገረዶች እግዚአብሔርን የማያውቁ ስለነበሩ፣ በእግዚአብሔር የተመ ረጠ ሕዝብ እናት ሊሆኑ እንደማይችሉ ተናግሮ ነበር፡፡ ስለዚህ እኔን ፍለጋ፣ አብርሃም ኤሊዔዘርን መስጴጦምያ ወዳለው፣ ወደ ካራን ላከው፡፡ ልብ አድርግ፣ የሚፈልገው እኔን እንደነበ ረ አያውቅም፡፡

«እንዴ እማዬ ግራ እያጋባሽኝ እኮ ነው፡፡»

በዚህ ጊዜ ርብቃ ሳቋ መጣ፡፡ «አብርሃም ኤሊዘርን ወደ አያትህ የባቱኤል ከተማ ላከው፤ ከረዥም ጉዞ በኋላ ኤ ሊዔዘር ከውኃ ጉድጓድ ከበጎች መንጋ ጋር አገናኝ፡፡ ውኃ እንዳጠጣው ጠየቀኝ፤ አንድ ጊዜ ሰጠሁትና አስገራሚ ቃላት ተናገርኩ እና ፍለጋው በዚሁ አበቃ!»

«አይ እማዬ፣ ታሪኩን በደንብ መንገር አለብሽ» አላት ያዕ

ቆብ፡፡ አንድ ጊዜ ደግሞ ጣፋጭ የሆነውን ወጡን አማሰለው፤ አሁንም የነጭ ሽንኩርቱ ሽታ ያውዳል፡፡ «እውነትም አስገራሚ ቃላት!» ብሎ ፈገግ አለ፡፡

ድንገት ውሾቹ ጮኹ፤ ዶሮቹ አሽካኩ፤ ከፍተኛ የጩኸት ጥሪ ተሰማ- እነሆ ዔሳው በራፉ ላይ ቆሞአል፡፡

«ምን እየተቀቀለ ነው ደግሞ እዚህ?- ሂድ ውጣ አንተ ውሻ!» አንዱ ውሻ አለቀሰ፤ ሌላው ደግሞ ጮኸ፡፡ አዎን፣ ዔሳው ቆሟል፤ ጸጉሩ ጭፍርር ብሎአል ደግሞም በጭቃ ተ ለውሶአል፡፡



«ምን እየተቀቀለ ነው?» አለና ዔሳው ተመለከተ ከዚያም የያዕቆብን የድስት ክዳን ከፈተው።

«ኦ፣ ያዕቆብ ከዛ ቀይ ወጥህ እስቲ ትንሽ ስጠኝ። ርቦኛል። አሁን ካልበላሁ መሞቴ ነው! ደኅና ምግብ ከበላሁ ብዙ ቀናት ሆኖኛል። ትንሽ ስጠኝ ጐሽ! ልሞት ትንሽ ቀርቶኛል።»

«እንዴታ ዔሳው» አለ ያዕቆብ፤ «እንደ ፈለግህ እሰጥሃለሁ። አንተም አጸፋውን ብኵርናህን ትሸጥልኛለህ።»

«ኦ ያ የተባረከው ብኵርና ! አንተ በአእምሮህ ብኩርና አለ። እኔ በራብ እየሞትኩኝ የሚያስደስት ነገር ምን ይጠቅመኛል? ላየው እችላለሁ? ልበላው እችላለሁ? ባዶ የሆነውን ሆዴንስ ሊሞላልኝ ይችላልን? አንተን የሚያስደስትህ ከሆነ ይህ ከንቱ የሆነውን ነገር ውሰድልኝ እና «ምግብ ስጠኝ» ብሎ ኤሳው ጮኸ።

«ቃል ትገባልኛለህ?»

«እንዴ ስማ እስቲ! ምን ቃል መግባት ያስፈልጋል? ከዚያ ቆንጆ ቀይ ወጥ በሰሐን ሞልተህ ስጠኝ እንጂ በዓለም ያለውን የማይረባ አሮጌ ብኵርና ሁሉ ውሰድ። አዎን እምልልሃለሁ።»

ያዕቆብ ከወጡ እየጨለፈ ለዔሳው ሰጠው፤ እስኪጠግብ ድ ረስ ደግሞ ደጋግሞ ሰጠው።

«ግሩም የሆነ ነገር ነው ያዕቆብ!»

«አዲስ ሙሉ ልብስ እሠፋልሃለሁ ዔሳው፤ የምትቆይ ከሆነ እኔና ዲቦራ ለክተን እንሠፋልሃለን» አለችው ርብቃ

ለዘብ ባለ አንደበቷ። ከዚያ በኋላ ዔሳው በአደን የገደላትን እንስሳ ቆዳ ለመግፈፍ ወጣ። ሌሎች ከአደን የያዛቸው እንደ አጋዘን፣ የሜዳ ፍየል እንዲሁም ዳክየዎች ነበሩ። ወዲያውኑ የእነዚህን እንስሳት ቆዳዎች ገፈፈና እንዲደርቁ ከዛፎች ግንድ ላይ ሰቀላቸው።



«ጉበዝ ልጅ ያዕቆብ!» አለችው  እናቱ ለብቻቸው ሲሆኑ። «ጉበዝ ልጅ! አሁን ይኼ እርምጃ ቁጥር አንድ ነው።» ፈገግ እያለች ወደ ሽመና ሥራዋ ሄደች።

ዔሳው ብኩርናውን ሸጠው። እናም ያዕቆብ ወሰደው።

# 3

# «ጥል የለም!» (ፀብ የለም)

«ጌታዬ፣ ልንደበድባቸው አንችልምን? ልንደበድባቸው እንችላለን በል ጌታዬ:: እንደገና እነርሱ እኮ ናቸው- ፍልስጤ ማውያን:: የውኃ ጉድጓዶቻችንን ደፍነዋል፤ እንስሶቻችን በውኃ ጥም ሊሞቱ ነው፤ አንዳንዶቹም አስቀድመው ሞተ ዋል::

«እኔ የከብት እረኛህ ዲቅላህ ነኝ ጌታዬ፣ ከእኔ ጋርም ዮየቅታን አለ::» (የእግዚአብሔር ሕዝብ አለቃ የሆነውን ይስሐቅን ማነጋገር ልክ በስልክ እንደማውራት ነው:: ዓይኖቹ በደንብ ስለማያዩለት ተጨንቆና ትኩር ብሎ ሲያይ ማንነትህን መናገር አለብህ፤ ሰውን በድምፁ ለመለየት ጉበዝ ነበረና ነው::)

«እሺ ዲቅላህ፣ በድምፅህ አውቄሃለሁ» አለ አለቃው ይስሐቅ::

ዲቅላህ በጉንጩ ላይ ያለውን ደም በእጁ ጠረገ:: በጺሙ በኩል ደም ይንጠባጠብ ነበር:: ከግራ ዓይኑ ላይ ቁስል ነበ ረበት:: ዲቅላህ እየተናገረ ደሙን ለመጥረግ እጆቹን አሻሸ::

ዲቅላህና ዮቅታን ወደ ይስሐቅ ድንኳን ፈጥነው ገቡ:: ይስሐቅ በድንኳኑ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ያሳልፉ ነበር:: ነበ ረበት:: እንዲህ ለማድረግ የተገደደው በደንብ ስለማያይ ነበር:: ሰው ይዞት ካልወጣ ወደ ውጭ መውጣት አይችልም ነበረ::

«አይሆንም፣ አይሆንም ዲቅላህ» አለ ይስሐቅ። ፀብ ድብድብ የለም ብያለሁ፤ ይህንን ታውቃለህ። ፀብ የለም።»



«ነገር ግን፣ ጌታዬ፣ እነዚህ ፍልስጤማውያን ይህንን ሲያደርጉት ሦተኛ ጊዜአቸው ነው። ምስኪኖቹን እንስሶችህን ብታያቸው እኮ ጌታዬ፣ ምላሳቸው ደርቆ፣ አብጠውና በውኃ ጥም እያለከለኩ ነው፣ እነኛ መጥፎ ፍልስጤማውያን፡- «እናንተ የእግዚአብሔር ሰዎች ወደ አገራችሁ ሂዱ! አንፈልጋችሁም እዚህ እንድትኖሩ አንፈልግም ። በጎቻችሁንና መንጎቻችሁን ለእኛ ስጡን፤ እኛ እንጠብቃቸዋለን፤ እናንተ ግን ከአገራችን ውጡልን» እያሉ በመጮህ ይስቁና ይሳለቁብናል።»

«ድብድብ የለም፣ ዲቅላህ» አለ ይስሐቅ ረጋና ፍርጥም ብሎ።

«ነገር ግን ይህ ለሦስተኛ ጊዜ ነው ጌታዬ። ከሦስተኛ ጊዜ በኋላ  አሳብህን በእርግጥ መለወጥ አለብህ።» አለ ዲቅላህ ከጺሙ የሚንጠባጠበውን ደም እየ ጠራረገ። «ሁኔታዎች ነገሩን ይቀይሩታል ጌታዬ። ለእነዚህ ፍልስጤማውያን ደግሞ ይኸን ያህል!»

«ዲቅላና ዮቅታን አዳምጡ።» ዮቅታን የቀኝ እጁን እያሻሸ ነበር፤ በጣም አብጦ ነበር። «ምንም ቢሆን ሁኔታዎች ይለወጣሉ» አለ ይስሐቅ፤ «እግዚአብሔር ግን አይለወጥም። በአገራችን ራብ በመግባቱ በባዕድ አገር የምንኖር የእግዚአብሔር ሕዝብ ነን። የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ መሆናችን መጠን ደግሞ አንዋጋም አያችሁ? ዲቅላህ፣ ፊትህ ላይ የሚርፉትን ዝንቦችን እየገደልክ ነው? እጅህን በጣም ስታወዛውዝ አይሃለሁ።»

«አይደለም ጌታዬ፣ በፊት ላይ ያለውን ደም እየጠረኩ ነው። ዓይኔ ላይ ቁስል አለ። እነዚህ ፍልስጤማውያን! የዮቅታንንም እጁን ጐድተውታል።»

«ዲቅላህ፣ አልተጣላህም አይደል?» የይስሐቅ ድምጽ የደነገጠ ይመስላል፤ ይስሐቅ ብዙ ጊዜ አይበሳጭም።

«አዎን ጌታዬ። ፀብ የለም እንዳልክ እናውቃለን፣ ዳሩ ግን ወጣቱ ዔሳው ልጆችዎቿቸው ይቅመሱት አለን። እኛም ደግሞ ትንሽ ገረፍናቸው። እነዚህ ፍልስጤማውያን፤ እኛን

በኃይል በመግፋት የውኃ ጉድጓዶቻችንን ቆሻሻና በድንጋይ ሞሏቸው:: ስለዚህ ዋጋቸውን ሰጠናቸው:: ነገር ግን ወጣቱ ጌታ ያዕቆብ መጣና መደባደብ የለም ልጆች! ጌታው ይስሐቅ ፀብ የለም እንዳለ ታወቀላችሁ:: እኛ የእግዚአብሔር ሰዎች ነን፤ ታውቃላችሁ፤ ጌታው ይስሐቅ ደግሞ ፀብ የለም በሚለው ላይ በጣም የጸና ነው::»

«ወጣቱ ጌታ ዔሳው:- «ፈሪዎች! እነዚህን ፍልስጤ ማውያኝን ጠንከር አድርገን ብንምመታቸው ኖሮ መልካም ነበር:: ደኅና አድርገን ብንገርፋቸው እንደ በረገጉ ጥንቸሎች ተበታትነው ይቀሩ ነበር:: ይፈረጥጡ ነበር:: እኛ ከእነርሱ ይልቅ በጣም የበረታን ነን:: ይህን ነው ወጣቱ ጌታ ዔሳው ያለው::



«ነገር ግን ወጣቱ ጌታው  ያዕቆብ ሲናገር «ጥል የለም» ብሎአል። ስለዚህ እኛ ወደ ኋላ ማፈግፈግና ፍልስጤማውያኑ ደግሞ የፈለጉትን እንዲያደርጉ መተው ነበረብን። ወደ ውኃ ጉድጓዶቹ ቆሻሻና ትልልቅ ድንጋዮች እየወረወሩ ይስቁና ያሽካኩ ነበር። ለምስኪን እንስሶቹ የሚያስፈልግ በነበረው ንጹሕ ውኃ ውስጥ ድንጋይ እየገባ ሲያንቦራጭቀው መስማትና የእነርሱንም ሳቅና ማሽካካት አንድ ላይ ማዳመጥ በጣም የሚዘገንን ነበር።

«እኛ እረኞችህ ስለተናደድን ለመደባደብ የቀረን ትንሽ ነበር። እኔና ዮቅታን በመተባበር እንድንደበድባቸው እንድትፈቅድልን ልንጠይቅህ ወደዚህ መጠን ባንዴ ነው ከዚህ የምናባርራቸው ጌታዬ።» ዲቅላህ እየተናገረ ሳለ ከአፉ ደም ይንጠባጠብ ነበረ። ጥርሱ በሙሉ ደም በደም ሆኖ ነበር።

«ዲቅላህ፣ መልሴ አሁንም፤ አይሆንም ነው» አለ ይስሐቅ። «አሁንም ትእዛዜ ከዚያ ተነስታችሁ በተቻላችሁ መጠን ፈጥናችሁ ሌላ ጉድጓድ ቆፍሩ። ወጣቱ  ጌታ ያዕቆብ ጥል የለም ሲላችሁ ስሙት። እኛ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነን። እግዚአብሔር ይጠብቀናል።»

«ነገር ግን ጌታዬ ምስኪኖቹን እንስሶቹ ብታያቸው እኮ. . . ።»

«ሂድና ቊፋሮውን አስጀምረው ዮቅታን» አለ ይስሐቅ። «አንተ ግን ዲቅላህ ቊስልህን ብትንከባከብ ይሻላል።»

«እሺ፣ ጌታዬ ይስሐቅ፤ እንደ እርሱ አደርጋለሁ- ስለዚህ

እንድንጣላ አትፈቅድልንም ማለት ነዋ?»



«አልፈቅድም!»

ሁለቱ እረኞች ጥሉ ወደ ተፈጠረበት ስፍራ ሄዱ።

ርብቃ ይስሐቅን «ምን ነበር የሚሉት?» ብላ ለመጠየቅ መጣች።

«አይ፣ ያው የተለመደው የውኃ ጉድጓዶች ችግር ነው። ፍልስጤማውያኑ ጉድጓዶቹን ደፍነዋቸዋል። ከዓርባ ዓመታት በፊት አባታችን አብርሃም ያስቆፈራቸው ጉድጓዶች ነበሩ። ፍልስጤማውያን ደፍነዋቸው ነበር። ይሁን እንጂ እኛ ደግሞ አገኘናቸውና አፀዳናቸው። አሁንም ተደገመ። ፍልስጤ ማውያኑ በድጋሚ በቆሻሻና በድንጋይ እየሞሏቸው ነው። እንስሶቻችን በውኃ ጥም ሊሞቱ ነው» አሉ እነዲቅላህ። የእኛ ሰዎች እንዲዋጉ እንድፈቅድላቸው ይፈልጋሉ። ለዚህ ነው

እነኛ ሁለት ሰዎች መጥተው የነበሩ፡፡

«በመጨረሻ ደግሞ ግልፍተኛው ዔሳው ተዋጉ ቢላቸውም ያዕቆብ ግን እንዲያቆሙ ነግሮአቸዋል፡፡ ልባም ልጅ! እኔ፣ መንጋዎቹን ከዚያ እንዲያስለቅቁና ውኃ ያለበትን ፈልገው ጉድጓዶችን እንዲያስቈፍሩ ነግሬአቸዋለሁ፡፡ ዮቅታንና ጉድጓድ ቆፋሪዎቹ ይህንን ያደርጋሉ» ሲል ይስሐቅ ለርብቃ ነገራት፡፡

«እንዴት ትዕግሥተኛ ነህ ይስሐቅ፡፡ እነዚያ ፍልስጤማውያን ትምህርት ማግኘት አለባቸው፡፡ በብርታት እኛ ከእነርሱ በብዙ እንበልጣለን፡፡ አንዴ ብናሳያቸው ኮ ሰዎ ቻችንን አይነኳቸውም፡፡ እኔ ራሴ ሄጄ ልመታቸው እችላለሁ፡፡»

«ተይ ተይ፣ ርብቃ፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆናችንን አስታውሽ፡፡ ያለነው በባዕድ አገር ነው፤ ማለቴ የእኛ ባልሆነ መሬት ላይ ነን፡፡ እግዚአብሔር መሬት እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል- ጥሩ መሬት - ስለዚህ እግዚአብሔር ሰዎች እንዳልሆንን ዓይነት መሆን የለብንም፡፡

«በቤርሳቤህ እያለን ራብ ሲመጣብን ታውቂያለሽ» አለና ይስሐቅ ቀጠለ፤» ሁሉንም ወደ ግብጽ ለመውሰድ አስበን ነበር፡፡ በጎቹን፣ ከብጾቹን፣ ሕዝቡን፣ ጓዙን- ሁሉን ይዘን ወደ ግብጽ ለመሄድ ተዘጋጀን፡፡ ወደ ዚያው ደግሞ አመራን፡፡ ያኔ አንድ ሌሊት ነግሬሽ ነበረ ርብቃ- እግዚአብሔር እንዲህ እንዳለኝ «ይስሐቅ፣ ወደ ግብጽ አትሂድ፡፡ በጌራ አካባቢ ቆይ፡፡ ስለ አባትህ አብርሃምና ስለ ገባሁለት ቃል ስል

እጠብቅሃለሁ።» ስለዚህ የእኔ ውዷቷ ርብቃ፣ በእግዚአብሔር ከመተማመን በቀር ምን ማድረግ እችላለሁ? አንቺም ብትሆኚ ማድረግ ያለብሽ እንደዚሁ ነው።»

«አዎ፣ ቢሆንም ግን እነዚህ የፍልስጤኤም ሰዎች አንድ ትምህርት መማር አለባቸው» አለች ርብቃ።

«ያንን ትምህርት እንዳስተምር እግዚአብሔር አስተማሪ ካደረገኝ፣ እንዳስተምር ይነግረኛል። ነገር ግን አልነገረኝም።



«ርብቃ እውነት ቢሆንም ለመናገር ግን ያሳፍረኛል፤ ነገሩ እንዲህ ነው፡- አንቺ በተ መለከተ ስለዋሸሁት የፍልስጤ ማውያን ንጉሥ አቤሜሌክ ገሥጾኛል- ምክንያቱን ታውቂያለሽ አንቺን እኅቴ ናት እንዳልሁት። እኛ ወንዶች፣ በባዕድ አገር ሕይወታችንን ለማትረፍ ስንል ሚስቶቻችንን በተመለከተ የምንለው ነገር ነው፤ ለቆንጆች ሚስቶቻችን ሲባል እንዳንገደል እንፈራለን።

በእርግጥ ይህ ሁልጊዜ ውሸት አይደለም። አንዳንድ ሀብታም ውርሶቻቸውን ለማስቀረት ሲሉ ሚስቶቻቸውን እንደ እኅቶቻ ቸው ይቈጥሯቸዋል። እኔ ግን ንጉሥ አቤሜሌክን ማታለል

አልነበረብኝም» አለ ይስሐቅ:: «ያን ቀን ግን ስስምሽ ንጉሥ በመስኮቱ በኩል አይቶኛል አለ ይስሐቅ:: «በእርግጥ የይስሐቅ ሚስት መሆን አለባት:: እኅቱ አይደለችም! አለና አስጠርቶ ጠየቀኝ:: አንድ የሆነ ሰው ሳይድርልህ አይቀርም አለኝ ንጉሡ:: ያኔ ትልቅ ችግር ተፈጠረ:: ታስታውሻለሽ የእኛን ደኅንነት ለመጠበቅ ሲል ሕግ አወጣ::»

«ያልፈለግኩትን ያገባሁ ይመስል! » አለች ርብቃ:: «ባልሞክረው ይሻል ነበር እስከሚል አደርገው ነበር::»

«አዎ፣ ቆፍጣና ሴት ነሽ አንቺ:: አንቺነትሽን ትጠብቂ ነበር ብዬ ብገምትም ያ ዓይነት ነገር አጋጥሞናል፣ ለመኖር ያህል አልኩት:: እኅቴ ናት የሚያስብል ነገር ባይከሰትብን መልካም ነበረ:: የበለጠ እምነት ሊኖረኝ ይገባ ነበር:: ዳሩ ግን አንዳንዴ ከሚዛኑ ትንሽ ወጣ እንላለን:: በእግዚአብሔ ር ከመታመን ይልቅ ስለ አንዳንድ ነገሮች እንጨነቃለን:: የማይታወቅ ፍርሃት ነው:: ከእንግዲህ ወዲህ ግን ፍርሃትም ሆነ (ጠብ) አይኖርም:: መታመናችንን በእግዚአብሔር ላይ ስናደርግ ነፃ እንሆናለን::»



«ነገር ግን ከብቶቹ ውኃን ከየት ሊያገኙ ነው? እንስሶቹ ሁሉ በውኃ ጥም ቢሞቱሳ?»

«አይሞቱም። እግዚአብሔር ውኃ ያዘጋጃል። ዮቅታን በቅርብ ጊዜ ውኃ ያገኝልናል።»

ርብቃ «ይስሐቅ» ስትል ተጠራች። «በሞሪያ ተራራ ላይ አባትህ ለመሥዋዕት ሊያቀርብህ ሲል ተስፋ ቆርጠህ እንደ ነበር ሰዎች ይናገራሉ።»

በይስሐቅ ፊት ዝግ ያለ ፈገግታ ታየ። «ውዳቂ» አለ። «ፍጹም ውዳቂ አሳብ ነው!» እንዳውም እግዚአብሔር እውነት መሆኑን ያወቅሁት በዚያን ያችን ዕለት ነበር። ያችን ዕለት ነበር ደግሞ እግዚአብሔር ሲናገር የሰማሁት፤ በዚያች ዕለት እግዚአብሔር ኃላፊ መሆኑንና በነገር ሁሉ ጣልቃ ገብቶ መከልከልና መስጠት እንደሚችል ተማርኩ። እንዲህ ያለ ከንቱ ነገር የሚሰማ ታዲያ ማን ነው? በሞሪያ ተራራ ደግሞ እኔ ተስፋ ልቆርጥ!

«የተወደደው ሽማግሌ አባቴ አብርሃም በዚያች ዕለት ብዙ ነገር አስተምሮኛል። አቤት፣ እንዴት ያለ የእምነት ሰው ነበረ! «እግዚአብሔር አንተን ለእኔ ተስፋ ሰጥቶኛል» አለኝ። «አንተን ከእኔ ወስዶ ቢሆን ኖሮ፣ አንተኑ መልሶ ይሰጠኝ ነበ ረ። እግዚአብሔር የሞተውን ሊያነሣ ይችላል።» አለ ውድ የሆነው አባዬ። እኔም እርሱን አምነዋለሁ።

«ሰዎች የሚያዩ ይመስላሉ እንጂ ፈጽሞ አያስተውሉም። እግዚአብሔር «እባርክሃለሁ» ያለው ተስፋ ጸንቶ ይቆማል። ደግሞም «በምድር ያሉት ቤተሰቦች ሁሉ በአንተ አማካኝነት

ይባረካሉ»» ብሎታል።

«ይህ በልጅህ በዔሳው አማካኝነት እንደማይሆን የታወቀ ነው። የተመረጠው ያዕቆብ ነው።» አለች ርብቃ ዕድሉ እንዳያመልጣት።

ይስሐቅ ፈገግ አለ። «ስለዚህ ዔሳው ሊዋጋ ይችል ነበር?» እርሱ ደግ ልጅ ነው- ይሁን ብዙ የሚማረው ነገር አለ፤ አዎን ብዙ መማር አለበት።!»

«አስታውስ ይስሐቅ፣ ቦታህን የሚወስደው ያዕቆብ ነው» አለች ርብቃ ከድንኳኑ እየወጣች።

በዚያን ጊዜ የእረኞቹ ልጆች ቅልጥ ያለ ጨዋታ እየተ ጨዋቱ ነበር። ዮቅታንን እየጠበቁት ነበር። ዮቅታን ውኃ የሚገኝበትን ምርጥ ቦታ በመምረጥ ላይ ነበር።



ከዚያም ቦታው ተገኝቶ ምልክት ተደረገበትና ቆፋሪዎቹ መቆፈር ጀመሩ። አንዱ ቡድን ሲደክም፣ ሌላው ቡድን ይተካ ነበረ።

ቆፋሪዎቹ ሲቆፍሩ፣ ጕድጓዱ ጥልቅ እየሆነ፣ ጥልቅ እየሆነ ሄደ። የቈፈሩትን አፈር በማሰሮዎችና በባልዲዎች እየሞሉ፣ ታች ያሉ ሰዎች ላይ ላሉ ሰዎች ያቀብሏቸዋል፤ እነዚህ ደግሞ ዐፈሩን ያራግፉና ባዶ አድርገው እንደገና እንዲሞሉ ዕቃዎቹን ታች ላሉት ሰዎች ያቀብሏቸዋል። ሥራው እንዲህ እያለ ይካሄድ ነበር።

«ውኃው ይኸውና ተገኘ!» ብለው ተጣሩ ከታች ያሉት።

«ውኃ አግኝተዋል!» አሉ ላይ ያሉቱ ደግሞ፤ ከብት ጠባቂ ዎቹንና እረኞቹን ለማሰማት እየጮኹ።



ወዲያውም፣ ባልዲዎቹንና ማሰሮዎቹን በውኃ መሙላት ጀመሩ:: ወደላይ መሳብና ከአዲሱ ውኃ ጉድጓድ አፋፍ ላይ በተቀመጡ ገንዳዎች ውስጥ መገልበጥ ጀመሩ:: በዚህ ጊዜ እንስሶቹ የሚጠጣ ውኃ አገኙ:: ይስሐቅ ከድንኳኑ እየተንጐራደደ ሲወጣ ዜናውን ሰማ:: አለመታደሉ ዓይኖቹ በደንብ አያዩለትም ነበር:: በከፍተኛ ጥንቃቄ መራመድ ነበረበት:: ሰው አብሮት መራመድ የግድ ያስፈልገው ነበር::

ዮቅታን ዜናውን ሊያቀብለው ወደ እርሱ እየተጣደፈ ነበር:: «ጌታዬ፣ ኃይለኛ የሆነ የውኃ ምንጭ አግኝተናል:: ዘንድሮ የተሻለ የበቆሎ ምሪት ታገኛለህ:: (አዎን፣ የይስሐቅ ሕዝብ በቆሎ ያመርቱ ነበር፤ እንዲሁም ከፍተኛ ምሪት ያገኙ ነበር::) ከፍ ያለ ምርት ታገኛለህ ዘንድሮ ጌታዬ:: አምና እንኳ ከዘራኸው መቶ ዕጥፍ አግኝተሃል::»

ወደ ግቢው አንድ ሌላ ሰው ይመጣ ነበር- እንዳውም በፈረሶቻቸው እየጋለቡ ወደ ግቢው የሚመጡ ብዙ ሰዎች ነበሩ:: እየተጠጉ በመጡ ጊዜ ንጉሥ አቤሜሌክና የሠራዊቱ ሻምበል ነበሩ:: እና፣ ደግሞም. . .

«እስቲ ከአገሬ ውጡልኝ!» ሲል ጮኸ:: «ውጡ፣ ሁላችሁም! በዝታችሁብናል የበጎቻችሁም ብዛት መጠን የለውም:: ለራሳችን ውኃ እንፈልጋለን:: ስለዚህ ውጡልኝ፤ አለበለዚያ. . . !

# 4

# የውኃ ጉድጓድ! ጉድጓድ! ጉድጓድ!

መቼም ታላቅና ክቡር የሆነው የአብርሃም ልጅ ይስሐቅ፣ ንጉሥ «አቤሜሌክ፡- «ከአገራችን ውጡልን! በዝታችሁብናል፤ ውኃችንን ጨርሳችሁብናል፤ የቀረን ነገር የለምና ውጡልን!» ብሎ በጮኸበት ጊዜ የመለሰለት በትሕትና ነበር።

«እርግጥ ነው» አለ ይስሐቅ፤ «እንዳውም ስላስቀመጣችሁን እግዚአብሔር ይስጥልን» አለና አሳፈራቸው። ከዚህ በኋላ ከንጉሥ አቤሜሌክ ግዛት ነቅሎ እንዲወጣ ትእዛዝ ሰጠ።

«እንዴ! ያውላችሁ እንግዲህ የእኛው ጌታ በድጋሚ! ወጣት ጌታው ዔሳው ቢሆን ኖሮ ድብድብ እንድንገጥማቸው ይፈቅድልን ነበረ፤ እና አንድ ትምህርት እናስተምራቸው ነበር። ብዙ በመሆናችን ፈርተውናል። በቀላሉ እናሸንፋቸው ነበር» አለው ዲቅላህ ለዮቅታን።

ነገር ግን ቍጣቸውን በድንኳኑ ገመድና በተዘጋጀው ጓዝ ላይ ተወጡት። ዕቃውን ሲጭኑ በቡጢ፣ በርግጫ እየመቱ ፍልስጤማውያኑን የደበደቡ በማስመሰል! ንዴታቸው በረድ አለላቸው።



ያ ታላቅ ሕዝብ በፍጥነት ሊንቀሳቀስ አልቻለም። በመቶዎቹ የሚቆጠር ሕዝብ ትንንሽ ልጆችና አረጋውያን ነበሩባቸው። ደግሞም በሺዎች የሚቆጠሩ እንስሳት አህዮች፣ በጎች፣ ፍየሎችና ግመሎች ነበሩ። አንድ ቀን የፈጅ መንገድ ከተጓዙ በኋላ ግን ድንኳን ተክለው ሰፈሩ።

ውኃ መገኘት ስለነበረበት ዮቅታንና ጥቂት የውኃ ጉድጓድ ቆፋሪዎች ወደ ፊት ቀደሙ፤ ዮቅታን ውኃ ለመፈለግ፣ ሌሎቹ ደግሞ የውኃ ጉድጓድ ለመቆፈር።

ጥሩ የሆነ የውኃ ጉድጓድ ቆፍረው፣ እያንዳንዱም ነገድ ዕ ቃቸውን አራግፈው ለመቀመጥ እየተቃረቡ ሳለ፣ ወዲያውኑ የተናደዱ የፍልስጤም ከብት ጠባቂዎች መጡባቸውና፡- «ይህ የምትቀዱት ውኃ የእኛ ነው!» በማለት ጮኹባቸው።

ይስሐቅ ለከብት ጠባቂዎቹ እንዲተውላቸው ትእዛዝ ሰጠ፡፡ «ነገ ማለዳ እንቀሳቀሳለን» አለ፡፡ ያንንም ጉድጓድ ውኃ- «የቀጣ ጉድጓድ» ብሎ ሰየመው፡፡ ምናልባት ይስሐቅና ሕዝቡ ለጉድጓዱ ስም ስለሰጡት ትንሽ ሻል ሳይላቸው አለቀርም፡፡

ዮቅታንና የእርሱ ውኃ ጉድጓድ ቆፋሪዎች ወደ ፊት ቀድመው ሄዱ፡፡ አንድ የውኃ ጉድጓድ ቆፈሩ፤ ሰፋሪ ው ተንቀሳቅሶ አለፍ ብለው ድንኳኑን ተከሉ፡፡

ገና ደኅና ተመችቶአቸው እንደሰፈሩ፣ ሌላ ማን ይመጣል ሌሎች ተጨማሪ የፍልስጤም ከብት ጠባቂዎች እንጂ፡፡

«ውኃችንን እየሰረቃችሁ ነው! አገራችንን ውኃ እያሳጣችኁ ት ነው» ብለው ጮኹባቸው፡፡



ይስሐቅ ውድ ወገኖቼ በማለት ረጋ ባለ መንፈስ ነገ በጠዋት እንዲንቀሳቀሱ ለሕዝቡ ትእዛዝን አስተላለፈ። ይህን ጉድጓድ ደግሞ «የጭቅጭቅ ጉድጓድ» ብሎ ጠራው።

በእርግጥ እያንዳንዱ ሰው ለመንገድ ውኃ መያዝ እንዳለበት መቼም የታወቀ ነው።

ውኃ ፈላጊው ዮቅታንና ረዳቶቹ እንደገና ቀድመው ሄዱ። እነርሱ ከሰፋሪው ይልቅ ፈጥነው መሄድ ይችሉ ነበር። ውኃ አገኙና ሌላ የውኃ ጉድጓድ ቆፈሩ። ሕዝቡም ከጉድጓዱ ዙሪያ ሰፈሩ። የይስሐቅ ታላቁ ሕዝብ ሰፈራ አሁን ወደ ቤርሳቤህ ሊመለስ የቀረው ትንሽ ነው።

እና ብታምኑም ባታምኑም ይጮኹባቸው ዘንድ የመጣ አንድም ፍልጤኤም አልነበረም።

«መልካም በመጨረሻ» አለ ይስሐቅ፤ «ለእኛ የሚሆን ቦታ ተገኝ።» እና የቀረው ለጉድጓዱ ስም መስጠት ብቻ ነው። ሕዝቡ ይህንን እየጠበቀ ነው። ይስሐቅ ለጉድጓድ ያወጣለት ስም፦ «እነሆ አሁን እግዚአብሔር ሰፊ ቦታ ሰጠን፤ በምድርም ላይ እንበዛለን» ሲል «ሮሖቦት» የሚል ነበረ።



«በመጨረሻ ደህና ሆንን» አለ ይስሐቅ፤ «ወደ አገራችንም ቀረብን ሁላችንም ወደ ቤርሳቤህ ብንመለስ ይሻለናል» አለ። (መጀመሪያ ለመሰደድ የተነሡት ከዚህ ቦታ ነበር፣ ይህ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለቤተሰቡ እንደሚሰጠው ተስፋ የገባለት አገር ውስጥ የሚገኝ ነው፤ እነ ይስሐቅና ሰፋሪዎቹ ደግሞ የአብርሃም ቤተሰብ ናቸው።)

ልክ በዛች ሌሊት ይስሐቅና ተጓዦቹ ወደ ቤርሳቤ እንደተመለሱ እግዚአብሔር ተናገረው- በእርግጥም ተናገረው። «ይስሐቅ» አለው እግዚአብሔር፤ «እኔ የአብርሃም አምላክ ነኝ። ይስሐቅ በዚህ ጊዜ በፍርሃት፣ በደስታና በተመስጦ ተርበተበተ። የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት አንድ ነገር ነው!

«አትፍራ ይስሐቅ» አለው እግዚአብሔር። «እኔ ካንተ ጋር ነኝ፤ እባርክህማለሁ፤ ለባርያዬ አብርሃም ሲባል የታላቅ ሕዝብ መንግሥት ትሆናለህ።» (እግዚአብሔር ስለ አብርሃም ብዙ አስቦአል፤ አይደለም እንዴ? እግዚአብሔር አብርሃምን «ወዳጄ» እንዳለው እናነባለን።)



ያም ሆነ ይህ ይስሐቅ መንቀጥቀጡን አቁሞ በጣም ደስታ ፍስሐና መረጋጋት ተሰማው:: በመጀመሪያ ያደረገው ነገር ወዲያውኑ እዚያው ቦታ መሠዊያን መሥራት ነበረ:: የሚ ረዱት አገልጋዮችን ይዞ፣ ከሁሉ ምርጥ የሆነ በጉን መረጠና ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ:: እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበትና የሚያስደስትበት ሌላ መንገድ አልነበ ረውም::

ከዚህ በኋላ ዮቅታን እንደገና ውኃን ለማግኘት በርትቶ ፍለጋ ውስጥ ገባ:: ዮቅታን ላይና ታች ሲል ልጆች ይመለከቱት ነበር::

ዮቅታንም «እዚሁ ቆፍሩ!» ብሎ ሲጮህ ልጆቹ ይደነቁ ነበር:: ቆፋሪዎቹ ሲቆፍሩና ከባልዲው ዐፈሩን የሚገለብጡትን ሰዎች ማየት ደስ ይላቸው ነበር:: በመጨረሻ ባልዲዎቹ ወደ ጉድጓዱ ሲለቀቁ የመንቦጫረቅ ድምፅ ሲሰማ ቆፋሪዎቹ ወደ ላይ በገመድ እየተሳቡ ይወጡ ነበር:: ምክንያቱም ውኃው ከቁርጭምጭሚታቸው አልፎ ጉልበታቸው ድረስ ስለወጣ:: በዚህ ጊዜ ልጆቹ ይህንን በተመስጦ ሲያዩ፣ ወደ ቤ ት ሄደው ራታቸውን መብላት እንኳ ይረሱ ነበር::



ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ድንኳኑን መትከል እንደ ጀመረና ዕቃውን እንደ ዘረገፈ ማንም ሳይሆን ከንጉሥ አቤሜሌክ የተላከ መልእክተኛ ብቅ አለ።

«ምንድን ነው አሁን ደግሞ/ ከግዛቱ ወጥተንለታል» አሉ።

ከንጉሥ አቤሜሌክ ወደ አለቃ ይስሐቅ የተላከ መልእክተኛ! አለቃው ይስሐቅ ግን በጣም ተረጋግቶ ነበረ። መልእክተኛውም፡- «ንጉሥ አቤሜሌክ መጥቶ ሊያይህ ይፈልጋል» አለው። ይስሐቅም፡- «በእርግጥ ለእራት እንዲመጣ ንገረው። ዕቃዎቻችንን ገና አላዘጋጀንም፤ ቢሆንም «ወደ እራት ጥቂት ጓደኞቹንም ይዞ እንዲመጣ ንገረው» አለው።

መልእክተኛውም ሄደ። በማግሥቱ መልእክተኛው ተመልሶ መጣና፣ «ንጉሥ አቤሜሌክ፡- «በጣም አመሰግናለሁ፤» ብሎሃል ወደ እራቱ መምጣት ደስ ይለዋል። ከቅርብ ጓደኞቹ መካከል አንዱ የሆነውን የሠራዊቱን አለቃ ይዞ ይመጣል። ሌሎችም አብረውት የሚመጡ ይኖሩ ይሆናል» አለ።

«ርብቃ!» ሲል ተጣራ ይስሐቅ፤ «ንጉሥ አቤሜሌክና የሠራዊቱ አለቃ እንዲሁም ሌሎችም ጥቂት ሰዎች ዛሬ እዚህ ይመጣሉ። ከእኛ ጋር ለመብላት ተስማምተዋል። ስለዚህ ያ ልዩ የሆነ ጣፋጭ ወጥሽን ሥሪ፤ እነኛን አባዬና እማዬ ከዑርና ካራን ያመጧቸውን የቤተሰባችን የወርቅና የብር ሳሕኖቻችንን እንጠቀማለን። ደኅና አድርገን እንዘንጥባቸዋልን። እኔ ደግሞ የክብር ካባዬን እደርባለሁ።»

«አይ አንተ- ይስሐቅ! ሰላም ፈጣሪ አይደለህ! ይህ እንኳ ለእነርሱ አይገባቸውም። ነበር ዳሩ ግን አንተ እንዳልክ ይሁን። በድርድራችን ላይ ያዕቆብን ሳትፈልገው አትቀርም። ዔሳው ብቻ ቢሳተፍ ለእነርሱ ደስ እንደሚላቸው ሰምቻለሁ። በዔሳው ዙሪያ ሚሥጢር ሊጫወቱ ይችላሉ። ነገር ግን ያዕቆብ የድርድሩ የመጨረሻ ውጤት ምን እንደሚሆን አሳምሮ ያውቃል። በድርድሩ እርሱን አይፈልጉትም። ይህም ማለት አንተ መያዝ ያለብህ እርሱን ነው።»

«እንዴታ በዚህ ስምምነት ላይማ ያዕቆብን እፈልገዋለሁ:: እርሱ መቼ መናገርና መቼ ደግሞ አፉን መሰብሰብ እንዳለበት ያውቃል:: ምስኪን ዔሳው! ልበ ቅን ልጅ:: አፉን ይከፍትና እግሩን



ይጨምርበታል- አንዳንዴማ ሁለት እግሮቹን:: ምስኪን ልጅ! እርሱም እዛው ሊገኝ ይችላል፤ ዳሩ ግን እንዳይናገር እከለክለዋለሁ::»

«ይስሐቅ በዚህ ጊት ዔሳውን በተመለከተ ቁም ነገር እየተናገርክ ነው:: እስቲ ልጠይቅህ ለመሆኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ ሊሆን የሚችለው ከቶ እንዴት ሆኖ ነው? የማይቻል ነገር ነው! እርባና የሌለው! መሳቂያ!

«ነገር ግን፣ አሁን ስለዚህ ጉዳይ የማውሪያ ጊዜ አይደለም:: ለማንኛውም እርሱ የእግዚአብሔር ምርጫ ነው ብሎ ማሰቡ ሞኝነት ነው:: በማንኛውም ነገር እግዚአብሔር የሚለው:- «ያዕቆብ» ነው:: ይህንን ደግሜ ደጋግሜ ነግሬሃለሁ:: ዳሩ ግን አሁን ስለዚህ ጉዳይ ማውሪያው ጊዜ አይደለም:: ዛሬ ላንተ ከንጉሥ አቤሜሌክ ጋር መደራደር፣ ለእኔ ደግሞ ድግስን ማዘጋጀት ነው:: እግዚአብሔር ይርዳን::»



ይስሐቅ የክብር ልብሱን ለባበሰ:: ርብቃ ለጥብስ የሚሆነውን የፍየል ሥጋ እንዲያዘጋጁ ገረዶቿን በሥራ ጠምዳቸዋለች፤ ሌሎቹን ደግሞ የሚጠጣውን ነገር እንዲያዘጋጁ መድባቸዋለች፤ ሌሎቹም ወርቃማ መጠጫ ዎች (ዋንጫዎች)ና ብርማዎቹ መቅጃ (ጆኮች) እንዲሁም የብር ጕድጓድን ሳሕኖችን ለፍራ ፍሬዎችና ለኦቾሎኒ ማስቀመጫ እያወጡ ይወለውሏቸዋል:: ጥቂቶቹ ሠራተኞች ደግሞ ምርጥ የሆነ ፍራፍሬና አትክልት ለመግዛት ቤርሳቤህ ወደሚገኘው ገቢያ ስፍራ ሄደዋል::

ያዕቆብ ከበጎቹ ማደሪያ ወደ እናቱ ድንኳን መጣ:: ምንድን ነው እማዬ? ማን ሊመጣ ነው?»

«ንጉሥ አቤሜሌክና የሠራዊቱ ሻምበል እንደዚሁም ጥቂት ወዳጆቹ ይመጣሉ::»

«የሚመጣው በሰላም ነው?»

«ተስፋ እናደርጋለን:: አባትህ እንዲሁ አስቧል:: ንጉሥ አቤሜሌክ ከአባትህ፣ ከአንተና ከዔሳው ጋር ለመብላት ተ ስማምቶአል::»

«ድግሱን ማዘጋጀት እኔ እረዳሻለሁ እማዬ::»

«አይደለም አይደለም ልጄ፤ አንተ ምርጡን ልብስህን ለባብስ:: አንተ በድርድሩ ላይ መገኘት አለብህ::»

«ኦፍ አይሆንም እማዬ:: እኔ የበኩር ልጅ አይደለሁም:: የአባዬ ቀኝ እጅ ዔሳው ነው:: ብኩርናውን የሸጠልኝ ቢሆንም እንኳ ምንም ለውጥ አላመጣም:: አባቴ ዔሳው ብኩርናውን እንደሸጠልኝ እውቅና ለመስጠት ደንታ የለውም::»

«ስማ ልጄ፤ ዛሬ ማለዳ አባትህ አንተ ከንጉሥ አቤሜሌክ ጋር በሚደረገው ስብሰባ ላይ እንድትገኝ እንደሚፈልግ ነግሮኛ ል:: «ያዕቆብ አርቆ የማሰብ ጥበብ አለው» ብሎአል:: «ማንም ያዕቆብን ማደናገር አይችልም:: ዔሳው አፉን ከፍቶ እግሩን ይጨምራል - ያውም ሁለት እግሮቹን! የለም፣ አባትህ «ያዕ ቆብ መቼ መናገርና መቼ ደግሞ አፉን መዝጋት እንደሚገባው ያውቃል» ብሎአል:: «ስለዚህ ያዕቆብ ከእኔ ጋር መኖር አለበት» ብሏል:: ዔሳውም እዛው ይገኛል፤ ሆኖም ግን እንዳይናገር አባትህ ይከለክለዋል:: የእግዚአብሔርን ሕዝብ የምትመራ በእርግጥ አንተ ትሆናለህ:: ምንም ቢሆን ምን አንተ ለመሆንህ ከመወለድህ በፊት እግዚአብሔር ነግሮኛ

ል::»

«ነገር ግን አባዬ ኮ ለዚህ እውቅና አይሰጠውም እማዬ::»

«አሁን ሄደህ ተዘጋጅ ያዕቆብ፤ እና ወደ አባትህ ድንኳን ሂድ:: የንጉሡ መምጫ ቀርቧል፤ አባትህ ደግሞ ንጉሡ ከመምጣቱ በፊት በአንዳንድ ነጥቦች ከአንተ ጋር ሊወያ የሚፈልግ ይመስለኛል::»

«ማን ነህ? ያዕቆብ»



ያዕቆብ ወደ ድንኳኑ እንዲገባ ይስሐቅ በደከሙ ዓይኖቹ ልጁን ሊያየው ሞከረ:: የይስሐቅ ዓይኖች ሁኔታ እንዴት የሚያሳዝን ነው:: በይስሐቅ ዘመን የዓይን መነፅር የሚያዙ የዓይን ዶክተሮች አልነበሩም:: መነፅር ቢያገኝ ኖሮ ለይስሐቅ እንዴት በጠቀመው! በኋላ ታሪ ኩን እንደምንሰማው እንጂ ለይስሐቅ የዓይን መነፅር ታዝዞለት ቢሆን ኖሮ በሕይወቱና በሌሎች ሰዎች ሕይወት ላይ ምን ያህል ለውጥ ያመጣ ነበር!

«አባዬ እኔ ያዕቆብ ነኝ::»

«እንዴ፣ ያዕቆብ! ዛሬ እንግዶች ይመጡብናል:: ንጉሥ አቤ

ሜሌክ የሠራዊቱ አለቃ ዋና አዛዥ ምናልባትም ሌሎችም ሊመጡ ይችላሉ» አለ ይስሐቅ::

«በሰላም ይመጣሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ አባዬ::» አለ ያዕ ቆብ

«እኔም እንደዛ አስባለሁ ያዕቆብ:: ከእኛ ጋር አብረውን ለመብላት ተስማምተዋል፤ ይህ በራሱ መልካም ምልክት ነው:: እንደፈሩንም ፍንጭ ሰምቻለሁ:: ከፊል በረኻ በሆነው እርሻ ቦታ ያለው ብዙ ምርት -ዓምና እኛ እንዳገኘነው ዘንድሮ ደግሞ ከዘራው መቶ ዕጥፍ ጊዜ የሚያገኘው ማን ይሆን? የእኛ ስኬታማነት በማይታየው አምላካችን ላይ ጥለውታል፤ ይህም ሐቅ ነው:: ያንን የመሰለ ፍልቅልቅ ምንጭ እንድናገኝ የት መቆፈር እንዳለብን ያሳየን፣ እንደዚሁም እርሻዎቻችንን በመስኖ እንድናጠጣ ያደረገን እርሱ ነው:: አቤሜሌክና ሕዝቡ ግን ይህንን ሁሉ ያዩት በጥርጥር አስማታዊ ኃይል እንዳለን አድርገው ነው::»

«እንደዛው ሲያስቡ ይኑሩ!» አለ ያዕቆብ:: ይስሐቅ ሳቀ::

«አሁን እኛንና የማይታየው አምላካችንን እንደ ጠላቶች ሳይሆን፣ እንደ ተባባሪዎቻቸው ወይም ሸሪኮቻቸው አድርገው ነው የሚፈልጉን:: ፈርተውናል::»

«በዛው ይቀጥሉበት!» አለ ያዕቆብ:: ሁለቱም ደግሞ ሳቁ::

«አንተ በጣም ገራም ነህ አባዬ:: ለመብትህ ፍጹም አትታገልም::»

እኔ አደርገው ከምችለው በላይ የሚያደርግልኝና «የሚዋጋልኝ አምላክ እያለኝ እኔ ለምን እታገላለሁ?

ወዲያውኑ ንጉሥ አቤሜሌክ ደረሰ። ሠራተኞቹ እግር የማጠቡን ሥራ አከናውነው፤ የሰላምታ ልውውጥ ተካሄደ።



ይስሐቅም፡ «ግርማዊነትዎን በማየቴ ደስ ብሎኛል፤ እንደዚያ አድርገው ከአገርዎ ካስወጡን በኋላ እኔን ለመጠየቅ በመምጣትዎ ተገርሜአለሁ!።»

እራቱ ትልቅ ስኬት ነበር። ግሩም ምግብ፣ ጣፋጭ ፍራፍሬዎች፣ መጠጦች፣ ንግግሮች፣ ትረካዎች፣ መዝሙሮች ነበሩበት። እንግዶቹም እዛው አደሩ።

በማግሥቱ ጠዋት እያንዳንዳቸው መሐላ አደረጉ፤ በአለቃው ይስሐቅ ሕዝብና በንጉሥ አቤሜሌክ ሕዝብ መካከል የሰላም ውል አትመው አጸደቁ። የንጉሡ ቤተሰብ

ደስ በሚል መንፈስ ወደ አገራቸው ተመለሱ::



እነርሱ እንደ ሄዱ፣ ወዲያውኑ ዲቅላና ዮቅታን ወደ ይስሐቅ ድንኳን እየሮጡ መጥተው:- «ጌታዬ አሁን በተቆፈ ረው ጉድጓድ አንድ በኃይል የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ አግኝተነዋል!» አሉት::

ይስሐቅ ደስታውን አልቻለውም:: የውኃ ጉድጓዱን:- «የመሐላ ጉድጓድ» ብሎ ስም አወጣለት:: እግዚአብሔርንም አመሰገኑ::

«አሁን ልጆች» አለ ይስሐቅ ፈገግ ብሎ፤ «የዛሬዎቹ ክንውኖች አለመጣላት የተሸለ እንደ ሆነ አያሳዩምን? ችግራችሁን ለእግዚአብሔር ንገሩትና እርሱ እንዲፈታው ተ ውለት!»

# 5

# እነዚያ ምራቶች!



«አይ . . . ይ፣ ይስሐቅ! አንድ አሠቃቂ ነገር ተከስቷል! የእኛ ወገን የሆነችው ሴት፣ ወንድ ልጇን ከሒታውያን ልጃገረዶች ጋር እንዲደባለቅና ወደ ሙሉ ጨረቃ በዓላቸው እንዲሄድ በመፍቀዷና ረገምኳትና ነገሩ እንዴት ዘግናኝ እንደሆነ ስነግራት እርሷ በትሑት መንፈስ «ወጣት ጌታው ዔሳው ነው እርሱን ሌሎች ወንዶች ልጆችንም ወደዛው የአምልኮት ሥነ ሥርዓት የወሰዳቸው አለችኝ» ርብቃ እያለቀሰች ስማኝ «ሴትዮዋ እንደ ነገረችኝ- ዔሳው ከሴቶቹ መሃል - ዮዲት የተባለች አሕዛብ ሴት ማግባቱን ነግራኛለች:: ያገባትም በምሥጢር ነበረ:: ከዚህ የተነሣ ዔሳውን ለአያሌ ቀናት እንዳላየነው አንተም ታውቃለህ:: ሴትዮዋ የልጅቷንም ስም ሳይቀር ነግራኛለች:: ሐፍረተቢስና ብልሳ ናጽም ብላለች:: በጣም ነው ያዘንኩት:: የገዛ ልጃችን ሄዶ አሕዛብ ሴት ካገባ፣ በጕሳ አባላት ላይ ምንም ሥልጣን አይኖ

ረንም:: አየህ ይስሐቅ!»

«ልጃችን አሕዛብ ሴት ካገባ ነው የምትዪው:: ደግሞም ያገባት በምሥጢር ነበረ ነው ያልሽው»

«አዎን አዎ፣ አግብቷል- ሴትየዋ ያለችው እንደዛው ነው:: ዔሳው ከአሕዛብ ወገን ሌላ ሴትም የሆነበት ምክንያት እርስ በእርስ የተጠባበቀ ኅብረት ካላቸው ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ብቸኛ አሕዛብ እንዳትሆን ነው:- በድንኳኗ ውስጥ ምስሎች አሉ፤ አለባበሷም ቢሆን አስነዋሪና ቅጥ ያጣ ነው::»

«ስላገባት ሴት ነው እያወራሽ ያለሽው ወይንስ ገና ወደ ፊት ስለሚያገባት?»

«ያገባትም የሚያገባትም ጓደኛሞች ናቸው:: ኧረ ምን ይሻላል ምን ይሻለናል?»

ይህ «እውነት ከሆነ፣ ገና ያልተከናወነውን ጋብቻ እቃወመዋለሁ::»

«አሃ፣ ዔሳው ራሱ ይኸውና፤ ብቻውን. . .

«ልጅ ዔሳው፣ ለብዙ ቀናት አላየንህም:: ይህ የምንሰማው ምንድን ነው? አሉባልታ ብቻ እንደሆነ ተስፋ እናደርጋለን::

ዔሳው በበደለኝነት ስሜት አባቱን ቀጥሎ እናቱን ይመለከት ጀመር::

«ዮዲት የምትባለዋን ሴት ታውቃለህ?» ብሎ ጠየቀው ይስሐቅ::



«ምነው፣ አዎን፣ ሚስቴ ናት። አይታችኋት የማታውቁ ከሁሉ ቆንጆ የሆነች ትንሽዬ ልጅ ናት። ባውቅ ኖሮ እንድትተ ዋወቋት አመጣት ነበር። ትናደዳላችሁ ብዬ ስለ እርሷ ምንም አልተናገርኩም። እኔ እንደ ሆነ ያለ እርሷ መኖር አልችልም። በጣም ውድ የሆነች ትንሽዬ ፍጡር ናት።

«በመሠረቱ፣ እርሷ ብቸኛ ናት። በነገዱ ውስጥ ያሉት ሰ ዎች ለእርሷ ጥሩ አይደሉም። ለምን እንዳገባሁዋት ያልታያቸው ከአንዳንድ ልጆች በስተቀር ሌሎቹ ሊያነጋግሯት እንኳ አይፈልጉም። እነርሱ ማግባት የሚፈልጉት ከነገዳቸው - ከአንድ ቦታ ብቻ ነው። ስለዚህ ዮዲት ብቸኛ ትሁን እንጂ ብቸኝነቷ ለአጭር ጊዜ ነው። ባሼማት የተባለች ጓደኛዋን

አገባለሁ:: እርሷም የሒታዊው የኤሎን ልጅ ናት:: ሠርጉ የሚከናወነው በሙሉ ጨረቃ ወቅት ስለሆነ እናንተም ብትገኙ መልካም ነው::»

ይስሐቅና ርብቃ የሚናገሩት ጠፋባቸው:: ርብቃ አንድ ነገር ለመናገር አፏን ብዙ ጊዜ ብትከፍትም ምንም ነገር መናገር አልቻለችም::

በመጨረሻ፣ ርብቃ ድንገት እንዲህ ስትል ተናገረች:- «አንተ ለታላቁ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ ለመሆን ተ መርጠሃል ብሎ ማሰቡ የማይቻል ነው:: ልክ በዚሁ ቀን ከነገዱ በሆነችው አንዲት ሴት ለመፍረድ ተጠርቼ ነበር፤ እና አንዲት አሕዛብ ሴት በምሥጢር ልታገባ እንዳሰብክ ወሬው በጆሮዬ ጥልቅ ብሎ ገብቶአል::»

በዚህ ጊዜ ርብቃ ራሷን በእጆቿ ይዛ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች::

ከዚህም በኋላ ይስሐቅ ተናገረ:: ሊታወሩ ከቀረቡት ዓይኖቹ ላይ እንባ ኰለል ኰለል አለ:: «ልጄ ሆይ፣ የሒታዊው የኤሎን ልጅ ከሆነችው ከባሽ- እ. እ ማን ነበር ያልካት ስሟን? ልታደርገው ያሰብከውን ጋብቻ መቃወሙ ግዴታዬ ነው:: በነገዴ ፊት እንደ አርአያ ሆኜ፣ ጋብቻችሁን ለመቃወም ግዴታ አለብኝ::»

«ግን እኮ አባዬ ሁሉ ነገር አልቋል:: በኤሎን አትክልት ስፍራ በሙሉ ጨረቃ በዓል ላይ ይከናወናል:: ድግሡ ተ ዘጋጅቷል ጥሪውም ተደርጓል::»

«እዚህም እዛም አይሆንም ዔሳው። እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት ገና አሁን ስለሆነ፣ አርአያ በመሆን፣ በታላቁ የእግዚአብሔር ሕዝብ ፊት ልቃወም ግድ ነው። የእግዚአብሔር የሆነው ሕዝብ ከአሕዛብ ጋር መጋባት ክልክል ነው።



«እኔም ሳልነግርህ የቀረሁት እንደምትቆጣ ስላወቅኩኝ ነው።» አለ ዔሣው።

«እና ስለዚህ ይህ ጋብቻ መከናውን የለበትም ዔሳው። ወደ ልጅቱ አባት ወደ ሂታዊው -ኤሎን መልእክትን እልካለሁ።»

ዔሳው በኃዘን የሚያለቅሱትን ወላጆቹን ትቶ በንዴት

ከድንኳኑ ወጣ።

«ቶሎ ብለህ ተቃውሞህን ወደ ልጅቱ አባት ላክ» አለች ርብቃ እየተንሰቀሰቀች። ይስሐቅም ተቃውሞውን አስይዞ አሽከሩን ወደ ሒታዊው ኤሎን መኖሪያ ላከ።

አባትዬው ይስሐቅን ወዲያውኑ ሊገናኘው ተነሣ። በጣም ተናድዶም ነበር።



«ውብ በሆነችው ልጄ ላይ ያለህ ተቃውሞ ምን እንደ ሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ፤ እናንተ ዕብራተኛ ወገን ናችሁ። ልጄ ባሴ

ማት በጣም ውብ እንደሆነችና የዚጉራት ቤተ መቅደስ አገልጋይ የመሆንም ዕድል የነበራት ነች፡፡ የአንድ ከበርቴ በኩር ልጅ፣ ማለትም ያንተ ልጅ ሚስት ብሆን በቂ ሀበት ይኖረኛል ብላ ነው እንጂ፣ ባይሆን ኖሮ ለቤተሰብ ከፍተኛ ሀብት የምታመጣ ልጅ ነበረች፡፡ ድሮም እኛ እርሷን መስማት አልነበረብንም፡፡ እንዲያገባት ለልጅህ መፍቀድም አልነበረብንም፡፡ ዳሩ ምን ይደረግ፤ የልጅቷ ልብ ወደእርሱ አደላ፡፡ የምመኝላት ደስተኛና እንድትሆን ነው፤ ምስኪን ልጅ፡፡ ያንተው መቃወም እንደ ሆነ ዋጋቢስ ነው፡፡ ዔሳው ዝግጅቱን ጨርሶአል፡፡ ሠርጉ ኬብሮን በሚገኘው፣ በወይን አትክልት በታዬ፣ በሙሉ ጨረቃ ይከናወናል፡፡

«ያንተ መቃወም እንደ ሆነ የማይገባ ነገር ነው፡፡ ልጄ ልጅህን ወደ ሃማኖቷ (እምነቷ) እንዳትለውጠውና የአባቶቹን ሃይማኖት (እምነት) እንዳይተው ፈርተህ ነው፡፡ እስቲ ልወቀው ይህ ምን ክፋት አለውና ነው? የአብርሃም አምላክ ከሂታዊያን አማልክት የሚበልጠው በምኑ ነው? እስቲ ንገ ረኝ፤ ልወቀው፡፡ በእርግጥ የእናተ እምነት በዔሳው ሕይወት ስር የሰደደ ስለሆነ ልጄን እምነቱን ሊያስተምራት ይፈልግ ይሆናል፡፡ እስቲ እርሱ ይለውጣት! ይህንን እንደማልቃወም የዓለም ሁሉ አማልክት በሆኑት እምላለሁ፡፡ ሕዝባችን በዘረኛ ትዕቢታችሁና በትምክህተኛ ሃይማኖታችሁ እስከ ሞት ነው ያንገፈገፈው ልንገርህ፡፡»

ይስሐቅና ርብቃ ይህንን ሲሰሙ በጣም ደነገጡና አዘኑ፡፡

«ዓላማችን ምን እንደሆነ ለእነዚህ ሰዎች ለማስረዳት

የማይቻል ነው» አለ ይስሐቅ በኃዘን:: «ይኸ የዘረኝነት ትምክሕት አይደለም፤ የአብርሃምን አምላክ ያህቁን ማመን እንዳይበከል ንጹሕ አድርገን ለመያዝ እየሞከርን ነው:: ሂታዊው ኤሎን እንደሚለው ከሆነ የሚሉት፣ አየሽ ትክክለኛ ው አቋማችንን ብንነግራቸውም እነዚህ ሰዎች የሚረቱልን አይመስሉም:: ዔሳው ከሚያየውና ከሚያደርገው አልፈው የሚደረዱትና የሚያዩት አይመስሉም:: ስለዚህ፣ በእርግጥ ሠርጉ ሊካሄድ ነው:: እኛ ልናደርገው የምንችለው ቅንጣት ያህል ነገር የለም:: እኛ በሕጎቻችን ባለመጽናታችን የእነዚህ አሕዛብ መሳለቂያ ልንሆን ነው:: ዳሩ ግን እኔ ተቃውሞዬን አሰምቻለሁ::»

«አዎን፤ ነገር ግን አሁን የበኵር ልጅህ ያልታዘዘህ ነው የሚመስለው» አለችው ርብቃ:: ከእንግዚህ በነገዱ ላይ ምንም ሥልጣን ላይኖርህ ነው:: አንተ ተቃውምህ የማትታዘዝ ከሆንህ ካለመቃወም አይሻልም በራስ መተማመንህን ልታጣ ነው:: ወይኔ. . . ወይኔ. . . «በራስ መተማመንን ማጣት ቁም ነገር አይደለም «ዋናው ነገር መቃወሙ ነው» ሲል መለሰ ይስሐቅ:: ይህ የእግዚአብሔርን መለኪያ በሕዝቡ ዘንድ የተ ጠበቀ ያደርጋል:: ዝናዬን ማጣቴ በእርግጥ ክብሬን ሊቀንስ እንደሚችል ጥርጥር የለውም:: ነገር ግን የእግዚአብሔር መለኪያዎች በሕዝቡ ዘንድ ሊጠበቁ ይገባል::

ያዕቆብ ከበጎቹ ማጕሪያ ሲመጣ፣ ወላጆቹ በኃዘን ተ ኵራምተው አገኛቸው:: የርብቃ ዓይኖች በልቅሶ ምክንያት አባብጠውና ቀልተው ነበር:: የይስሐቅ የታወሩ ዓይኖች

ደግሞ ቁልጭልጭ ብለው ፊት ለፊቱ አፍጥጠው ነበር፡፡



«ምንድን ነው ነገሩ፣ አባዬና እማዬ ምን ሆናችሁ? አሟችኋል እንዴ?» አለ ያዕቆብ

«አዎን፣ ልባችን ታምሟል፡፡ ይህ በሕይወታችን ውስጥ ከሁሉ የከፋ ቀን ነው፡፡ ያዕቆብ፤ ዔሳው አሕዛብ ሴት ሊያገባ የመሆኑ ምሥጢር ተገልጦአል፡፡»

«ምን? በውኑ አድርጎታልን? የሚያደርገው አይመስለኝም ነበር፡፡ ከእነርሱ መሃከል ጓደኞች እንደነበሩት ባውቅም የፓትሪያርኩ ይስሐቅ ልጅ አሕዛብ ሴት ያገባል ብዬ አስቤ

ውም አላውቅ። እና አሁንም ነገዱን እንደሚመራ ይታሰባልን?»

«አሁን ያዕቆብ ከዚያ የበለጠ ነገር አንተ ታውቃለህ» አለችው ርብቃ። ይህንን ስትል፣ የርብቃ ድምጽ የተለየ ትርጉም ነበረው።



«ቃል ግባልን ያዕቆብ፤ ከኔ ወገን ከሆነው ሕዝብ፣ ወደ ሰሜን ፓደናራም ሄደህ ሚስት እንደምታገባ ቃል ግባልን። አንድ ቀን ያዕቆብ፣ ወንድሜ ላባ ወዳለበት ስፍራ ሄደህ ሚስትን ከዚያ መፈልግ አለብህ። ያዕቆብ አሕዛብ ሴት ካገባህ እኔ በኃዘን እሞትብሃለሁ።»

«እኔ እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ አላደርግም፣ እማዬ። እኔ ከሁሉ በላይ የምፈልገው እግዚአብሔርን ማገልገል ነው፤ እኔ የምፈልገው እግዚአብሔርን እንዳገለግል የምትረዳኝ ሚስት ነው እንጂ የምታደናቅፈኝ» አይደለም።

የዔሳውና የባሼማት ሠርግ ኬብሮን በሚገኘው፣ በአባትዋ የወይን አትክልት ስፍራ፣ ሙሉ ጨረቃ በወጣችበት ሌ ሊት ተከናወነ። ይስሐቅና ርብቃ ወደ ሠርጉ አልሄዱም። ጊዜ ውን ያሳለፉት በቤታቸው፣ በኃዘንና በትካዜ ነበር። ይህ መጥፎ ምሳሌ በነገዳቸው ወጣቶች ላይ የሚያሳድረውን ተ

ጽእኖ፣ እግዚአብሔር ያግደዋል ብለው ተስፋ አደረጉ::

ከዚያ በኋላ ዔሣው ወደ ቤቱ ብዙም አልመጣም፤ ሁለቱ ሚስቶቹም ጭራሽ መጥተው አያውቁም:: ድንኳኖቻቸው ሩቅ ነበሩ:: በድንኳኖቿቸው ውስጥ ምስልና ጣዖት እንደነበሩ፣ በሂታዊያን አማልክት ክብር ተብሎ በሚደረገው ግብዣም ይገ ኙ እንደነበር ተነግሮአል:: ምስኪኖቹ ይስሐቅና ርብቃ በጣም አዝነዋል::

አንድ ቀን ግን ዔሳው ወደ ወላጆቹ ድንኳን መጣ:: ሽማግሌ ዓይነ- ስውር አባቱ የልጁን ድምፅ እንደገና ሲሰማ ማልቀስ ቃጣው::

«ዔሣው፣ ልጄ፣ ና እስቲ ከጎኔ ተቀመጥ:: እዚህ ከመጣህ ረዥም ጊዜ ሆኖሃል:: ስለምትወድደው አደን ቁጭ ብለን ካወራን ረዥም ጊዜ ሆኖአል:: እያደንክ ስታበላኝ የነበረውን ጣፋጭ ሥጋም ከበላሁ ቆይቻለሁ:: ሳስበው አፌ ምራቅ ይሞላል:: እያደንክ ከምታመጣው የፍየሎች ሥጋ የበለጠ ጣዕ ም ያለው ነገር የለም::

«ቀኖቼ አጭር እንደ ሆኑ ይሰማኛል ዔሳው:: እምብዛም የምቆይ አይመስለኝም:: ከመሞቴ በፊት ልባርክህ እፈልጋለሁ:: ስለዚህ ቶሎ ሄደህ የአደን ሥጋ ለምን አታመጣልኝም? በደንብ ጥበስልኝና አብረን ተቀምጠን እኔ ከሥጋው እየበላሁ እባርክሃለሁ::»

«እንዴታ አባዬ:: ሁለት ቀን ይወስድብኝ ቢሆንም እንጂ አንተን ካስደሰተህ ደስ ብሎኝ እሄዳለሁ::»



ርብቃ ይህንን አጭር ጭውውት አደመጠች።

«ይስሐቅ ያሰበው ይኖር ይሆን?» አለች ራሷ ለራሷ። ያዕ ቆብንም ለማግኘት ፈጥና ሄደች።

«ያዕቆብ፣ ያዕቆብ፣ አባትህ አብዷል መሰለኝ። መሆን አለበት! ስማኝ። ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርግ። ዔሳው ዛሬ እዚህ ነበር። ቀስቱንና ፍላጻውን ይዞ አሁን ሄዶአል። አባትህ የፍየል ግልገሎች ሥጋ አድኖና ከሽኖ እንዲያበላውና ከዛም እንደሚባርከው ነግሮታል። ይህም ባርኮት ለበኵር ልጅ የሚሰጥ ነው። በቅርብ እንደሚሞት ይናገራል። ይህን ዕ ቅዱን ማቆም አለብን! ስማኝ!»

# 6

# እናት ትፈልገው የነበረውን አገኘች!

ለታላቁ ልጅ የሚሰጠውን፣ የወራሽ ባርኮት ይስሐቅ ለዔሳው እንደሚሰጠው ቃል ሲገባለት በሰማች ጊዜ፣ ርብቃ በጣም ደነገጠች:: «ከአደንህ ሥጋ አምጣልኝ ዔሳው» አለ ይስሐቅ፤ «እኔ ደግሞ እባርክሃለሁ:: በቅርብ እሞታለሁ::» ይህ ባርኮት ዛሬ እንደኑዛዜ ነው፤ ማንም ደግሞ ሊለውጠው አይችልም::

«ያዕቆብ፣ ስማኝ» አለች ርብቃ «ወደ መንጋዎቹ ቶሎ ሂድ:: ሁለት ጠቦት ፍየሎች አምጣልኝና ለአባትህ የሚጣፍጥ አድርጌ እሠራለታለሁ- ልክ እንደ ዔሳው አድርጌ:: ድሮስ ቢሆን፣ እርሱን ያስተማርኩ እኔ አይደለሁ:: እራቱን እኔ እሠራለሁ፤ አንተ ደግሞ ባርኮቱን ታገኛለሁ::»

«ዳሩ ግን እኔ ለማየት ያልቻልኩት እንትን--»

«ስማ ያዕቆብ:: ጊዜ እየገደለን ነው ያለነው:: እኔ ለአባትህ እራቱን እሠራለታለሁ፤ አንተ ደግሞ ትወስድለታለህ፤ ለዔሳው ሊሰጠው ያሰበውን የበኵር ልጅ ባርኮት ትቀበላለህ:: አንዴ ካገኘኸው ካንተ፣ ፍጹም ካንተ የሚወስደው ከቶ አይኖርም:: ያዕቆብ፣ አብዛኛውን ጊዜ ገለጻ የሚያስፈልግህ ልጅ አይደለህም:: ጊዜውን እያባከንን ነው::»



«ዳሩ ግን እማዬ፣ እኔ ዔሳው እንደሆንኩ ሊገምት እንዲችል የምናደርገው በምን ዓይነት መንገድ ነው? እራቱን ስወስድለት፣ እኔ የምወስድለት ከሆነ ማለቴ ነው፣ ያዕቆብ መሆኔን በድምፄ ያውቀኛል:: እጆቼን፣ አንገቴን ሊዳብሰኝ ይችላል- ዔሳው ጸጉራም ነው፤ እኔ ግን ጸጉር የሌለኝ ልሙጥ ነኝ::

ርብቃ ኮስተር ብላ በሹክሹክታ እየተናገረች ትኩረት ለመስጠት እጆቿንም እየተጠቀመች ያዕቆብ ያለችውን እንዲፈጽም ከድንኳኑ ወደውጭ አወጣችው::

«አንተ በመጠንም በቅርጽም ልክ እንደ ዔሳው ነህ:: በእርግጥ በድምፃችሁ ብተለያዩም ብዙ አይደለም:: አባትህ

እጆችህንና አንገትህንም ቢዳብስህ፣ በርግጥ ዔሳው ጸጉራም ነው፤ ሻካራም ነው፤ ለዚሁም የፍየል ቆዳ በእጆችህና በአንገትህ ባድርግልህ አሞኝነው ማለት ነው። የዔሳውን ልብስ ትለብሳለህ። የእርሱ ጥቂት ልብስ እኔ ጋ አለ።

«በል ሂድና ፍየሎቹን አምጣልኝ። ቶሎ በል ያዕቆብ! የምንሠራው ሥራ የተሳካ እንዲሆንልን የምናደርገውን ሁሉ ማወቅ አለብን።»

«ነገር ግን እማዬ እኔ ላደርገው አልችልም። አባዬ ከነቃብኝ ይረግመኛል እንጂ አይባርከኝም።»

«ያአንተ ርግማን ለእኔ ድርገው ያዕቆብ። አሁን ሂድና ከመንጋው ለይተህ ፍየሎቹን አምጣ። እኔ እዚህ አዘጋጃለሁ። ለዲቦራም እንኳ አንነግራትም። ተንኰሉን የምናውቀው እኔና አንተ ብቻ እንሆናለን። ቶሎ በል!»



ያዕቆብ ሄደ። ከመንጋው ሁለቱን የፍየል ጠቦቶች እየመ ረጠ ያዕቆብ የእናቱን ዕቅድ ያሰላስል ነበር። በእርግጥ፣ የነገዱ ቀጣይ መሪ ሊያደርገውና እግዚአብሔር ለአብርሃምና ቀጥለው ላሉት ወራሾቹ ያወጀውን (የተናገረውን) ባርኮት ምርቃት ሊያስገኝለት የሚችለው የማረጋገጫ ዘዴ ይህ ብቻ ነበረ።

በኋላ ቆየት ብሎም ቢሆን ያዕቆብ ባርኮቱን የማግኘቱ ጉዳይ እግዚአብሔር ራሱ እንደሚያከናውነው ያዕቆብና እናቱ አስበውበታል። አሁን ግን፣ እናቱ እንዳለችው ጊዜን ማባከን የለባቸውም ነበር። ነገሩ ሆነ ቀረም አሁን ነው።

ባርኮቱን ፈጥኖ መንጠቅ ካልሆነ ግን ለዘላለም የዔሳው ይሆናል። ዔሳው ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት ብቃቱም የሌለው ሰው ነበር። ይህንን ማንም የሚያውቀው ነበር- ነውረኛ መንገዱንና የሂታዊያንን አማልክት የሚያመልኩና ምስሎች የነበራቸውን አሕዛብ ሚስቶቹንስ ምን ደርጋቸዋል? ይሁን እንጂ እግዚአብሐር ጣልቃ ገብቶ፣ የታላቁ ነገድና የእግዚአብሔርን ሕዝብ መሪ የሚያደርገውን አዋጅ ወስዶ ለያዕቆብ የመስጠቱ ጉዳይ ምንም መንገድ ያለው አይመስልም ነበር፡፧

በእርግጥ እግዚአብሔር በመጨረሻዋ ደቂቃ ጣልቃ ገብቶ ይስሐቅ በሞሪያ ተራራ ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት እንዳይሆን አቁሞአል። ያዕቆብ ታሪኩን ሰምቶታል፣ የሆነውንም ያውቃል) በእርግጥ ጉዳዩ የእግዚአብሔርና የአብርሃም ጉዳይ ነበር፧ ይኸውም፡- አብርሃም ከይስሐቅ ይልቅ ለእግዚአብሔር ቅርበት እንደነበረው ገመተ። ለማንኛ

ውም ሁሉም ተብሎ ከተከናወነ በኋላ፣ አሁን መዘግየቱ ብልህነት አልነበረም። ጉዳዩ በጣም አስጊ ነው። እናትየዋ ግን በደንብ ይዛው ነበር።

ያዕቆብ እስካሁን ጠቦቶቹን ገፍፎና ብልት ብልት አዘጋጅቶ ጨርሶአል። ወደ እናቱ ድንኳን ሲሄድ እናቱ በዓለም ካለ ወጥ ሁሉ የላቀ ጣእም ያለው ወጥ ልትሠራበት ያዘጋጀቻቸው ቅመማ ቅመሞችና ነጭ ሽንኩርት ሸተተው። ከምድጃው የሚመጣ የዳቦ ሽታም ነበር።

«መቼ ትመጣለህ ብዬ ስጨነቅ ነበርኮ ያዕቆብ» አለችው።

እንቅስቃሴዋ ሁሉ ፈጣን ነበረ። እሳቱ እንዲቀጣጠል ቈሰቈሰችው። ሁለቱም ርብቃና ያዕቆብ በሥራ ተጠምደው አሁንም በሹክሹክታ ያወሩ ነበር።

የተቈራረጠውን ለስላሳ ሥጋ እያገላበጡ በቅቤ ደኅና አድርገው ጠበሱት። ተጠብሶ ቈንጆ ቡናማ በሆነ ጊዜ ቅጠላ-ቅጠሎቹንና አትክልቱን ጨምረውበት እንዲበስል ተውት። የርብቃን ምርጥ የሆነ ቤት የተጠመቀ ወይን አመጡ። ደግሞም ዓፈር ዓፈር የሚሸተውን የዔሳው የግብርና ልብስም ቀረበ። በያዕቆብ እጆችና አንገት ላይ የሚደረገው የፍየል ቆዳም ተዘጋጀ።

የያዕቆብ ሥጋት ከባድ ነበር። በዚህ መሃከል መንትየው ወንድሙ ዔሳው የመጣስ እንደሆነ? ግን አይሆንም። እርሱ አንዳንድ ጊዜ ለብዙ ቀናት ያህል የበረኻ ፍየሎችን ለማደን ይሄዳል። የለም፤ እርሱ ለዘመናትም የሚመጣ አይደለም።

አባትየው ይስሐቅ፡- «ይህ ወጥ ከበረኻ የፍየል ሥጋ የተ ሠራ አይደለም» ያለስ እንደ ሆነ? ምን መልስ ይሰጠዋል? ያዕ ቆብ መልሱን ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ እንዲህስ ቢሆን. . .? እንዲህስ ቢሆን. . .?

ያዕቆብ ብዙ ሊባሉ የሚችሉትን ነገሮች አሰበ፡፡ ብዙ ተ ጨነቀ፤ ዘና ሊልም አልቻለም፡፡



እናቱ ተስፋ ቈረጠች፡፡ መንትየዎቹ ሳይወለዱ እግዚአብሔ ር፡- ትንሹ መንትያ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመራ ይሆናል ያላትን እንዲያከናውን እግዚአብሔርን መርዷቷ ነው አይደል? ይህንን የመጨረሻ ዕድሉ የሆነውን የአባቱን ባርኮት በመጨረሻ ደቂቃ ያዕቆብ ካልጨበጠው፣ ሁሉም ነገር ጠፋ

ማለት ነው- ለዚሁ ስትል በአገሯ በፓዳናለም የተወችው ነገር ሁሉ መና ሆኖ ቀረ ማለት ነው። አደገኛ ነገር ነበር፤ ቢሆንም ሊወሰድ የሚገባው ነገር ነበረ። (ርብቃ እግዚአብሔርን በተ መለከተ ያላወቀችው አንዳንድ ነገሮች ነበሩ፤ አልነበሩም እንዴ? ወደ አንድ አቅጣጫ የሚገፋ አይደለም፤ ነው እንዴ?) ለማኛውም ትክክለኛውን ነገር እያደረገች ለመሆኗ እርግጠኛ ነበረች።

እስካሁን ያዕቆብን በዔሳው ልብስ አበጃጅታዋለች። በኋለኛ ው እጆቹ የፍየል ቆዳ እንደ  የእጅ ጓንቷ አድርጋለታለች- በአንገቱም እንደዚሁ። ሥጋው፣ ጣፋጩ ዳቦና ወይን ጠጁ ትሪ ላይ ተደርጓል- ያዕቆብ ደግሞ ትሪውን  ተሸክሞ ወደ ይስሐቅ ድንኳን ሄደ።



ርብቃ ሁሉንም ውጭ ሆና በድብቅ ታደምጥ ነበር።

«አባዬ!»

«አቤት ልጄ። ማንው አሁን ወደዚህ የመጣው? የይስሐቅ ዓይኖች ድምፅ ወደ ሰማበት ዞሩ።

«አባዬ እኔ የበኩር ልጅህ ዔሳው ነኝ፣» ሲል ያዕቆብ ዋሸ። እንዳመጣልህ የጠየቅኸኝን ሥጋ አምጥቼልሃለሁ። አባዬ ና፤ እኔ ከመባረክህ በፊት ብላና ደስ ይበልህ።»

«ቶሎ መጣህ ልጄ። ከአደንህ እንዴት ቶሎ መጣህ?»

«አይ፣ ዛሬ ቶሎ የመጣሁት እግዚአብሔር ዛሬ እንስሳቱን በቶሎ በመንገዴ ላይ ሳይሰድዳቸው አይቀርም። ቀላል አደን ነበር።»

«ና እስቲ ወደ እኔ ጠጋ በል ልጄ። በእውነት ልጄ ዔሳው መሆንህን ወይም አለመሆንህን ማወቅ እፈልጋለሁ። ባርኮቱን ለመስጠት ሰው ጥንቃቄ ማድረግ አለበት!»

ያዕቆብ መርበትበቱን ለመቈጣጠር ምን ያህል የጣረ መሰላችሁ!» ርብቃ ከውጭ ሆና ከንፈሯን እየነከሰችና እጆቿን እያሻሸች ታዳምጥ ነበር፤ በኃይልም ተጨነቀች።

«መልካም፣ መልካም፣ እጆቹስ የዔሳው ናቸው፤ ድምፅህ ግን ዛሬ በጣም የያዕቆብን ይመስላል። እንደ ዓይን -ብርሃኔ፣ የመስማት ኃይሌም እንዳልተሳሳተብኝ ተስፋ አደርጋለሁ። አዎን፣ አዎ፣ የዔሳው እጆች ናቸው። ልብስህ የእርሻና የጥሩ ዓፈር ሽታ ይሸተኛል። ይቅር በለኝ ልጄ፤ ይቅር በለኝ፤

ባርኮቱ በጣም አስፈላጊና በጣም ሰፊ ስለሆነ ትክክለኛው ለሆነው ሰው ለመስጠት ማረጋገጥ ስላለብኝ ነው። እራቱን አምጣልኝ እስቲ፤ ልብላና እባርክሃሁ።

ያዕቆብ እንደ አፍ ማበሻ ያለ ጨርቅ በአባቱ አንገት ላይ አደረገለት። ዓይነ ስውር እንደነበር ታስታውሳላችሁ፤ ትንሽ መረቅ ተፈናጠቀበትና ትንሽዬ ሥጋ ከአጥንቱ ተላቃ በጭኑ ላይ ልትወድቅ ስትል ሊያያት አልቻለም።

«እሰይ እሰይ፤ በልብስህ ላይ ግሩም የሆነ የቀይ ዓፈርና የእርሻው ሽታ ይሸትተኛል ልጄ።» አለና ይስሐቅ እራቱን ደስ ብሎት በላ። አጥንቶቹ በተረፈው የሳሕን ምግብ ላይ እንዳይደባለቅ መሬት ላይ ጣላቸው።



ያዕቆብ እስኪጨርስ ድረስ መጠበቅ አቃተው፡፡ ዔሳው ለአባቱ ሥጋ ወጡን ይዞ ከመምጣቱ በፊት ባርኮቱ ቶሎ እንዲከናወን ፈለገ፡፡

ሽማግሌው አባቱ መጨረሻዋን ጠብታ መረቅ በዳቦ እየጠራ ረጋት እያለ ያዕቆብ እየተመለከተው ተጨነቀ፤ ፈራም፤ የሚያደርገውም ጠፋበት፡፡

«አቤት! ዔሳው ልጄ» አለ ይስሐቅ፤ «እንዳንተ አድርጎ የሥጋ ምግብ መሥራት የሚችል ከቶ የለም፡፡ ጠጋ በልና እስቲ ሳመኝ አሁን፤ እኔ ደግሞ ባርኮቱን እሰጥሃለሁ፡፡» አለ ይስሐቅ ደስ ያለው ይመስላል፡፡



ከውጭ ሆና በማዳመጥ ያለችው ርብቃ፣ በደስታ ልትጮህ ትንሽ ቀራት፡፡ እነዚያ ዓመታት፣ አዎን እነዚያ ዓመታት ተ ስፋ ያደረገችባቸው፣ የተመኘቻቸው ይህን ጊዜ ነበር፡፡

«ልብስህ እግዚአብሔር እንደባረከው መልካም እርሻ መሬት እንደሚሸትት፣ እግዚአብሔር የሰማይ ጠል፣ የመሬቱ ሀበት፣ እንዲሁም እህልና ወይን ጠጅ (ምግብና መጠጥ) አብዝቶ ይስጥህ፡፡ ሕዝቦች ያገለግሉሃል፤ መንግሥታትም ይሰግዱልሃል፤ ወንድሞችህም ቤተሰብህም ሳይቀሩ፡፡ የሚ ረግምህ ሁሉ የተረገመ ይሁን፤ የሚባርክህም ሁሉ ይባረክ፡፡»

«ያዕቆብ ለማለት የቻለው «አመሰግንሃለሁ አባዬ» ብቻ ነበር፡፡ ይህንን ብሎ ባዶውን ትሪዋው ይዞ ወደ እናቱ ድንኳን ተመለሰ፡፡

«ዋው»

«አገኘው» አለች ርብቃ፡፡ የደስታ እንባ በጉንጮቿ ላይ ዱብ፣ ዱብ እያሉ፡፡ ያዕቆብ ግን በቀዝቃዛ ላብ ተጠምቆ ነበረ፡፡ ጫካውን ገና አላለፉትም፡፡

በዚያን ጊዜ፣ ከርብቃ ድንኳን አጠገብ ማን ያለፈ መሰላችሁ- ወደ ውስጥ አላየም እንጂ- ዔሳው ነበረ፡፡ እርሱም ትሪውን ተሸክሞ ወደ ይስሐቅ ድንኳን አመራ፡፡

አዳምጡ!

«አባዬ በተቻለኝ መጠን ቶሎ መጥቻለሁ፡፡ ሥጋውን እድንኳኔ ውስጥ አዘጋጅቼዋለሁ፡፡ አባዬ ይኸው አሁን ብላና

ባርኮትህን ስጠኝ::»

ነገር ግን የይስሐቅ የታወሩ ዓይኖች ፊት ለፊቱ አፈጠጡ፤ እጆቹም የወንበሩን ጕኖች እንደጨበጡ፣ ይስሐቅ እየተንቀጠቀጠ «አንተ ማን ነህ?» አለ::

«ዔሳው ነኝ አባዬ፣ የበኵር ልጅህ! ሥጋ እንዳመጣልህ ነግ ረኸኝ ነበርኮ፣ ታስታውሳለህ? በእርግጥ አትረሳውም:: ተረጋጋ አባዬ:: ታስታውሳለህ አይደል? አትፍራ እኔ ነኝ! ይልቁንስ ብላ:: ጥሩ ነው:: ድሮ የማመጣልህና በጣም የምትወድደው የእኔው ምግብ ነው:: ወይንም አለ ብላ እንጂ አባዬ::»

ዳሩ ግን ይስሐቅ ገና ይንቀጠቀጥ ነበር:: «የት -የት- የት ነው ያ ሥጋ ያመጣልኝ ሰው? በልቻለሁ ኮ፣ ባርኬውማለሁ:: አዎን ሆኗል፤ ልመልሰው አልችልም::»

«በእርግጥ አባዬ እያለመ ነው!»

«በልቻለሁ፣ ጠጥቻለሁ ባርኬውማለሁ ባርኮቱን ሰጥቻለሁ» አለ::

የተጋጡ አጥንቶች ደግሞ በድንኳኑ ወለል ላይ ነበሩ::

እናም ዔሳው በሰፈር ያሉት ሁሉ እስኪሰሙት ድረስ ምርር ብሎ እያለቀሰ እንዲህ ሲል ለረዥም ጊዜ ጮኸ:- «እኔንም ባርከኝ እንጂ አባዬ:: ለእኔ የሚሆን ባርኮት የለህምን?»

«ወንድምህ አታልሎኝ ለአንተ ያልኩትን ባርኮትን/ ወስዶብሃል::»

«ይኸ ውሸታም! ይኸ አታላይ! በትክክል ነው «ነጣቂ»!

የተባለው:: ሁለቴ አታልሎኛል:: በመጀመሪያ በኵርናዬን ሰርቆብኛል:: (የለም፣ የለም ዔሳው፣ በግድየለሽነት በኵርናህን ሸጠኸለታል!)፤ አሁን ደግሞ ባርኮቴን ወስዶብኛል::»

ዔሳው እንደ ሕፃን ይንሰቀሰቅ ነበር::

«ለእኔ ምንም የቀረ የለም አባዬ? ትንሽ ባርኮት እንኳ?»

«ዔሳው ያዕቆብን ያንተ የበላይ አድርጌዋለሁ፤ ቤተሰብህ እርሱን ያገለግላል:: በእህል፣ በወይን ጠጅና በመልካም ነገሮችም ሁሉ ባርኬዋለሁ:: ኦ፣ ምን ልበልህ ልጄ?»



«አባዬ፣ እኔንም ባርከኝ። እባክህን፣ እባክህን እኔንም ባርከኝ። ለእኔ የሚሆን ምንም አልተረፈህም?»

«በሰይፍህ ትኖራለህ ዔሳው። ለወንድምህ ተገዥ ትሆናለህ። ነገር ግን አንድ ቀን፣ አንድ ቀን ከእስራቱ ትፈታለህ።»

ዔሳው እንደ ትንሽ ልጅ አለቀሰ፤ አባቱም አዘነለት።

ከዚያም ተነሣና ወጥቶ ሄደ። ከአባቱ ዓይን ተሰወረ። ጥርሶቹን እያፋጨ፣ እጆቹንም እየጨበጠ፦ «ያዕቆብን እጠላዋለሁ! እጠላዋለሁ! እጠላዋለሁ! አባዬም ከሞተ በኋላ- ብዙም አይቆይ ይሞታል- ያዕቆብን እገድለዋለሁ፤ እገድለዋለሁ፣ አዎን እገድለዋለሁ!» አለ።



በእርግጥ፣ ዔሳው በጣም ተናድዶ ነበርና ማንም እንዲሰማው ባይፈልግም እንኳ በታላቅ ንዴት በመጮኽ ማድረግ ያሰበውን ሲናገር አንዳንድ ሰ ዎች እንደ ነፋስ በጆሮአቸው ሽው አለባቸውና ሰሙት። የሆነ ሰው ደግሞ ሄደና ለርብቃ ነገራት።

ልክ በዚያን ጊዜ ያዕቆብ አልነበ ረም ቆየት ብሎ ግን መጣ። ርብቃም «ዔሳው በጣም ተናድዷል ያዕቆብ

ተጠንቀቅ! እገድለዋለሁ እያለ ነው፡፡ ፓደናለም (ካራን) ወደሚገኘው ወንድሜ፣ ወደ ላባ ቶሎ ብለህ ሂድ፡፡ እስክጠራህ ድረስ እዛው ቆይ፡፡ የዔሳው ቁጣ ሁሌ እንደሚበርድ፣ ቶሎ ይበርዳል፡፡ ሰላም ሲሆን ተመልሰህ እንድትመጣ አስጠራሃለሁ፡፡ አሁን ግን ለመሄድ ተዘጋጅ ያዕቆብ!» አለችው፡፡

«ስለዚህ ያዕቆብ ሻንጣውን ለማዘጋጀት ሄደ፡፡ ጧት በማለዳ ቤቱን ጥሎ መሄድ ይኖርበታል፡፡

# 7

# ነገር ግን ያገኝችውንም አጣችው

ያዕቆብ ሕይወቱን ለማትረፍ መሸሽ አለበት፡፡

ጉድ! ጉድ! ጉድ! በሕይወቱ ሙሉ የፈለገው  ነገር ነበረ- የነገዱ የተመረጠ መሪና ዋናው ወራሽ የመሆን - ይህንን እንዳገኘ ሁሉንም ትቶ መሸሽ የግድ ሆነበት!

ይህ የነገሮች መለዋወጥ ርብቃን አስደነገጣት፡፡ እርግጥ ያዕቆብ ሕይወቱን ለማትረፍ የግድ መሸሽ ነበረበት፡፡ ከዚህ በፊት ወንድሞች ወንድሞቻቸውን ገድለዋል፡፡ እስቲ አሁን የቃየን እና የአቤል ነገር ምን ይባላል? የእርሷ ያዕቆብ፣ የወደፊቱ የነገዱ ራስ የሚሆነው  መገደል የለበትም፡፡ በሚኮ ብለል ወይም ሕይወቱን ለማዳን በሚጠፋ ማንኛውም ሰው ምክንያት ዝናን ማጣት የለበትም፡፡

ርብቃ ጉበዝና ብልህ ሴት ነበረች፡፡ ቀጥላ ምን እንዳደረገች ታውቃላችሁ? ይስሐቅን ለመጠየቅ ሄደች፡፡ አታምኑኝም እርሱ ገና ይንቀጠቀጥ ነበረ፡፡ እርሷም አሕዛብ ስለሆኑት ሰል ዔሳው ሚስቶች አንሥታ ታወራለት ጀመር፡፡

«እነዚያ አሕዛብ ሴቶች» አለች፤ «ኑረዬን ዋጋቢስ አደረጉ እነዚህ አሕዛብ ከገቡ የእኔ መኖር ምንድን ነው!  ያዕቆብ አሕዛብ ሚስት ካገባ የእኔ መኖር ያከትማል»



ይስሐቅ አሁን ርብቃን እጅግ ወደዳት:: ውድና ጉበዝ ናት ብሎ አስቦ በጣም ወደዳት:: የእርሷ ክፉ ፍጻሜ ሊሰማ አልወደደም:: እርሷም ይህንን ታውቅ ነበረ!

«አዎን፣ ያዕቆብ አሕዛብ ሚስት አገባ ማለት እኔ በቃልኝ ማለት ነው! እኔን ካመጣህበት እርሱም ሚስት ቢያመጣስ ይስሐቅ::» አለች::

«አንዷን እንዲያመጣለት ማንን እንላክ ይሆን?» በሎ ይስሐቅ ጠየቀ:: «አባቴ አብርሃም አንቺን ለእኔ እንዲያመጣልኝ የላከው ሽማግሌውን ኤሊዔዘርን ነበር:: አሁን ግን ኤሊዔዘር ሞቷል:: አባቴ እንዳመነው እኔ የማምነው ሰው የለም::»

«አይ፣ ግን ኮ ያዕቆብን ራሱ ሄዶ ለእርሱ የምትሆነውን ያገኛል» አለች ርብቃ::

«መጀመሪያ፣ በጧት ያዕቆብ ወደ እኔ ስደጂው፤ እሺ ርብቃ?» አላት ይስሐቅ። አባቱ ሲልክበት ያዕቆብ ችግር ውስጥ የሚወድቅ መሰለው። ሻንጣውን አዘጋጅቶ ለመጨረስ የቀረው ትንሽ ነበር።



ስለዚህ ወደ ይስሐቅ ድንኳን ሄደ።

«ያዕቆብ» አለ ይስሐቅ፤ «አሕዛብ ሴት እድታገባ አልፈልግም፤ እናትህም በቀላሉ የምትሸከመው አይሆንም። ጉዳዩን አንሥተን ስንነጋገርበት ቆይተናል፤ እና ስለዚህ ወደ አጎትህ ላባ አገር ሄደህ ከአጎትህ ልጆች ሚስት ብትፈልግ መልካም ይመስለናል። ከእነርሱ አንዷን ምረጥና አግባ። ጌታም ይባርክህ፤ ብዙም ልጆች ይስጥህ። እግዚአብሔር

ታላቅና ብዙ ሕዝብም ያድርግህ:: እንዲሁም እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን በረከት- ለአንተም ለልጆችህም ይስጣችሁ:: ለአብርሃም ቃል የገባለትን አገርም ይስጣችሁ::»

ያዕቆብና ርብቃ ሊሰሙት የፈለጉት ትክክለኛ ባርኮት ይህ ነበር::

ሌሎች ሰዎችም ሰሙት::

ስለዚህ ያዕቆብ ዕቃውን አዘጋጅቶ ጨርሶ አባቱንና እናቱን ደኅና ሁኑ አላቸው:: እናቱን ግንደኅና ሁኚ ብሎ መሰናበቱን ጠልቶት ነበር:: ተሰናብቶ ሲሄድ ሰዎች አዩትና፤ መልካም እንዲሆንለት ተመኙለት::

ያዕቆብ ሚስትን ለመፈለግ ተጓዘ- ሕይወቱንም ለማዳን ጭምር!

ርብቃ ወደ ድንኳና ተመልሳ ገባች፤ እንባዋን ዋጥ አደ ረገችው:: ካለ ያዕቆብ ምን ታደርግ ይሆን?

«ይህ ምስክን ልጅ ደኅና እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ» አለች ብዙም ሳትጮኽ:: ርብቃ የተግባር ሴት ነበረች፤ ሥራ ፍጹም አትፈታም:: እንባዋን ዋጥ አድርጋ በሽመና ቦታዋ ተ ቀመጠች:: ለጥቂት ደቂቃ የሽመና ሥራዋን ሠራች:: እግሮቿን በመርገጫው ረግጣ አውታሩን ወደላይ ወደታች እያደረገች ሳለ መወርወሪያዋ ደግሞ ወደ ፊትና ወደ ኋላ እያለ በድሮቹ መሃል ይሽሎኰሎክ ነበረ::

ከዚያ አቆመች! ያ በሽመና ላይ ያለው ጨርቅ ለያዕቆብ

ሙሉ ልብስ ሲሆን የታለመ ጨርቅ ነበረ። አሁን ለሕይወቱ ሰግቶና ደንግጦ ከቤት ወጥቶ ሄዷል። ርብቃ ሌላ ክር መሸመን አልቻለችም። ከሽመና ቦታዋ ተነሣች።

ጥቂት ምግብ ማብሰል ነበረባት። ያዕቆብ ያችን የምሥር ወጥ ለመሥራት ሲዘጋጅ ድቅን አለባት። ሳሕኑ፣ ውኃው፣ ቀይ ምሥርና ሌላው ቅመማ ቅመም ሁሉ ተዘጋጅቶ ሽታው ሰፈሩን በሞላ ነቅንቆ፣ እዛ ያሉትን የራብ ስሜታቸውን የሚቀሰቅስ ወጥ ሲሠራበት ተደርድሮአል። ርብቃ መቀቀሉን ትታው ዘወር አለች፤ ምክንያቱም፣ ልትቋቋመው አልቻ ለችም። ርብቃ አሁን ልብስ ልትሰፋ ነው። የምትሰፋውን ልብስ ስታነሣ፤ ያዕቆብ ለመንጋዎቹ ሲሠራላቸው ያሰበውን የበረት ዕቅድና ንድፍ ተመለከተች ለአባቱና ለራሱ መንጋዎች ጭምር ማለት ነው። ርብቃ ላለማልቀስ ብትሞክርም አልቻ ለችውም። በከፍተኛው ስቅስቅ አለች፤ አሁንም፣ አሁንም አሁንም ስቅስቅ ስትል አለቀሰች።

በተሰበረ ልቦና በሃይል መንፈስ አለቀሰች። ያለ ያዕቆብ እንዴት ለመኖር ትችላለች?

አሮጊቷ ተንከባካቢ ዲቦራ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነበር ርብቃን ያገኛቻት ማለት ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ።

በዚያን ጧት ያዕቆብ ከቤት እንደ ወጣ፣ ከአንድ ወይም ሁለት ሰዓት በኋላ ማለት ነው፤ ዲቦራህ በተጨናነቀ ሁኔታ ውስጥ ርብቃን አየቻት። እርሷ ርብቃን ስትመለከታት በፊቷ ላይ ድፍረት የተላበሰች መስላ ታየቻት። ዳሩ ግን ዲቦራ የርብቃ ዓይኖች እንባ እንደቋጠሩ ተገንዝባለች። ከንፈሯንም ስትነክስ ተመለከታታለች።

ዲቦራ ወደ ርብቃ ድንኳን ቀስ ብላ ገብታ ከአጠገቧ ተቀመጠች፡፡ «ይገባኛል» ለማለት እጆቿን ይዛ እያሻሸች፣ ጨበጥ ጨበጥ አደረጋቻት፡፡



መጀመሪያ ላይ ርብቃ የበለጠ አለቀሰች፡፡ (ማስተዛዘን አንዳንዴ የተረሳውን ይቀሰቅስ የለ?) ነገር ግን ብዙ አልቆየችም ረጋ አለች፤ በመጨረሻ፡- «አመሰግናለሁ ዲቦራ የኔ ውድ ነርስ የጥንት ጓደኛዬ፡፡ መምጣትሽ መልካም ነው» አለች፡፡

«ዲቦራ» ስትል ጠራቻት ርብቃ፤ «የሰፈራችን ሰዎች፣ በግቢያችን ያሉት ሁሉ ያዕቆብ ለምን እንደ ሄደ ያውቃሉን?» ስትል ጠየቀቻት፡፡

«እንዴታ! ሁሉም ያውቃል እሜቴ» አለች ዲቦራ፡፡

«አቤት እንዴት የሚያሳዝን ነገር ነው!» አለች ርብቃ፡፡

«ምኑ ነው የሚያሳዝነው እሜቴ? ጌታዬ ይስሐቅ አንቺን ለመፈለግ ኤሊዔዘርን መላክ ብቻ ስለነበረበት ዕድለኛ ነበር፡፡ አሁን ግን ሄደው ለያዕቆብ ሚስት የሚያመጡለት እዚህ ኤ ሊዔዘሮች የሉም፡፡ ራሱ ሄዶ መፈለግ አለበት፡፡ ናፍቆሽ ይሆናል፤ ነገር ግን እሜቴ ቶሎ ይመጣልሻል፡፡ ኤሊዔዘር እንኳ አንቺን ፍለጋ ያን ያህል ጊዜ አልወሰደበትም፡፡» አለቻ ት ዲቦራ፡፡

«ዲቦራ፣ ወደ ድንኳኑ ሂጅና  በራፉ ላይ ሆነሽ ማንም ሰው ቆሞ ይሰማን እንደ ሆነ እይ፤ እሺ? ድንኳኑን ዙሪና ቆሞ የሚሰማን ሰው ካለ መጥተሽ  ንገሪኝ።»

ዲቦራ ሄደችና እንደተነገራት አደረገች። «አንድም ዝር የሚል ነፍስ የለም እሜቴ። ሁሉም ዛሬ ጧት በየሥራቸው ተሰማርተዋል። ለምን ይሆን?» አለች ዲቦራ።

«እንደዚሁ ተቻኩሎ ያዕቆብ ለምን እንደ ሄደ  በእርግጥ ማንም እንደማያውቅ እርግጠኛ ነሽ ዲቦራ? አንቺ ሁሉም ጋር ስለምትገናኚ ችግራቸውን ይነገሩሻል ብዬ አስባለሁ።ልክ እኔ የራሱን እንደነገርኩሽ ማለት ነው። እኔ ግን አምንሻለሁ። ነገር ግን ማንም ምን እንደማያውቅ እርግጠኛ  ነሽ ዲቦራ?»

«ማንም ሰው የሚያውቀው፣ ያዕቆብ ሚስት ለመፈለግ መሄዱን ነው። ይህ ደግሞ ምን ስሕተት አለው? እርግጥ ናፍቆሻል፤ ነገር ግን ቶሎ ተመልሶ ይመጣል እኮ።»



«አይመስልም!» አለች ርብቃ::

«አይመስልም?» ስትል ጠየቀቻት ዲቦራ::

«አዎን» ስትል መለሰች ርብቃ::

«አልገባኝም እሜቴ::» ዲቦራ ግራ የተጋባች ትመስላለች:: «አይመለስም?» ስትል ጠየቀች ዲቦራ:: «አዎን፤ እንደገና ፊጽሞ ላላየው እችላለሁ::» አለች ርብቃ::

«ምን!» አለች ዲቦራ::

«ዔሳው ሊገድለው አቅዷል» አለች ርብቃ::

«እንዴ፣ እሜቴ የምርሽ ነው እንዴ?» ስትል ጠየቀቻት ዲቦራ::

«አዎን፤ ያዕቆብ ባርኮቱንና፣ ወራሽነቱን ከአባቱ እንደ ተ ቀበለ፣ ዔሳው ሊገድለው ማሰቡን የሆነ ሰው ሰምቶታል:: ያዕ ቆብ ይህንን እንዲያገኝ አባትየውን ማታለል ነበረብን:: ዔሳውም በእርሱ ላይ በጣም ተናደደና አባቱ ሲሞት፣ ይህም ባጭር ጊዜ እንደሚሆንና ያዕቆብን እንደሚገድለው ሲናገር የሆነ ሰው ሰምቶታል::»

«ዔሳው እንደተናደደ ብዙጊዜ አይቆይም» አለች ዲቦራ:: እርሱ አሁን ሌላ ቆይቶ ሌላ ነው፤ ተለዋዋጭ ነው፣ እሜቴ፣ ዳሩ ግን ብዙም አይቆይም:: ወንድሙንም የሚገድል አይመስለኝም:: ያኔ ነገሩ በሚሆንበት ጊዜ ያስደነግጠው ይናል እንጂ ነገሩ ካለፈ በኋላ እንኳ የሚያደርገው አይመስለኝም» አለች ዲቦራ::

«እኔማ የዔሳው አደገኛ አዝማሚያ ካለፈ በኋላ እንደማስጠራው ለያዕቆብ ነግሬ ዋለሁ። ዳሩ ግን ዲቦራ፣ ትክክለኛውን ነገር ለማወቅ ጭልም ብሎብኛል። ፍጹም ይኸ ነው ለማለት አልችልም» ብላ እንደገና ርብቃ ተንሰቀሰቀች። «ያዕቆብን እንደገና የማያው በፍጹም አይመስለኝም። ሕዝባችን ደግሞ የወደፊቱ መሪያቸው ለሕይወቱ ሲል መሸሹን እንዲያውቁ አልፈልግም።

«ማንም እንዲህ የሚያስብ አይመስለኝም እሜቴ። በአእምሮአቸው ያለው ትልቁ ነገር፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚሆነው የተመረጠው መሪ ለእርሱ የምትስማማ ሚስት ለመፈለግ መሄዱን ነው። የዚህን አስፈላጊነትን ደግሞ ሁሉም ይገነዘቡታል። የጌታዬ ይስሐቅ ባርኮት ገና በጆሮቻቸው ውስጥ እያቃጨለ ነው። ፓትሪያርኩ ያዕቆብን ባርኮ ዛሬ ጧት ሲሰድደው ምን እንዳለ ሁሉም ሰምተዋል። በዚህ ጉዳይ መጨነቅ አያስፈልግሽም እሜቴ።

«ዔሳውም ቢሆን፣ እርግጠኛ ነኝ፣ ወንድሙ የሄደው ቢዚሁ ምክንያት ነው ብሎ ነው የሚያስበው። ያዕቆብ ከእርሱ እየሸሸ መሆኑን ዔሳው ፈጽሞ የማያውቀው ነገር ነው። እንዳውም ያዕቆብ ሲሄድ ሲያየው በጣም ነበረ ያዘነው። ያዕ ቆብ ልክ ከመሄዱ ቀደም ብሎ የአባቱን ባርኮት ሲቀበል ሰምቻለሁ። በመጨረሻ፣ ጌታዬ ይስሐቅ ትንሹ ልጁን የእግዚአብሔር ምርጥ መሆኑን እውቅና ሰጥቶታል ለካ ብዬ አሰብኩኝ- ይህም መንትያዎቹ ከመወለዳቸው በፊት ተነግሮሽ እንደነበር ነው እኮ እሜቴ። በመጨረሻ የልብሽ መሻት

ስለሆነልሽ እንዴት ተደስታ ይሆን ብዬ አሰብኩኝ። ጌታዬ ይስሐቅ ወራሽነቱን ለያዕቆብ መስጠቱ ግልጽ ነው።

«ዲቦራ፣ ለእኔ ሁሉ ነገር ደብልቅልቅ ብሎብኛል። የፈለግነውን አግኝተነዋል፤ ያገኘነው ግን በማታለል ነው። እግዚአብሔር ራሱ እንዲያደርገው መጠበቅ ነበረብን። አሁን የፈለግነውን አግኝተናል፤ ይሁን እንጂ ኃዘንም ተቀብለናል። ያዕቆብ ወራሽነቱን እንደተቀበለ፣ ለሕይወቱ ሲል መሸሽ ነበ ረበት- እያደረገ ያለውም ይህንን ነው።



«ዳሩ ግን ወንድምሽ እንዴት እንደሚቀበለው እኮ ደግሞ ማሰብ አለብሽ እሜቴ። ከአጎቱ ልጆች ጋርም መሆን እንዴት ደስ እንደሚለው አስቢ። አንድ ቀን ደግሞ ውብ ከሆነችው ሚስቱ ጋር ተመልሶ ይመጣል፤ እንደ አንቺ ዓይነት እንደምትሆን አምናለሁ እሜቴ። እግዚአብሔር የሰጠሽን ተ ስፋ ይጠብቃል። ያዕቆብ ሕዝቡን (ነገዱን) ይመራል አገሩንም

ይወርሳል። በይ ነይና ትንሽ ነገር እንቀማምስ ደስም ይበለን።»

ከዚያ በኋላ፣ ርብቃ ልታነጋግረው ወደ ይስሐቅ ሄደች።

«ዔሳው አልገባም ዛሬ» አላት። (ስለ ያዕቆብ ምንም ወሬ የለም።) «ዔሳው የት ይሆን ያለው?» አለ ይስሐቅ።

ዔሳው የት እንዳለ ማወቁ ያስገርመው ይሆናል።

ያዕቆብ በዚያን ጧት ሲሄድ ጊዜ፣ ዔሳው በአድናቆት ለአንድ ወይም ለሁለት ደቂቃ ያህል ቆሞ ነበር። ከእናቱ ወደ አባቱ፣ ከአባቱም ወደ እናቱ ይመለከት ነበር።



ይህ ሁሉ ለትክክለኛ ሚስት ተብሎ፣ የምትመች ሚስት! እናትና አባትስ ቢሆኑ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ሳይታወቅና አንድ ቀን እንኳ ለአደን ወጥቶ የማያውቅ፣ ያንን ያህል አደገኛ ጉዞ ብቻውን እንዲጓዝ፣ ያውም ሚስትን ለማግኘት ሲባል ያዕቆብን ሲለቅቁት ተዘጋጅተውና አስበውት ይሆን?

ደግሞም ሩቅ ከሆነው መስጴጦምያ ከተባለው አገር ከሚገኘው የቤተሰብ ወገን መሆን አለባት ብለዋል። ጉድ፣ ጉድ. . .።

ዔሳው ተደነቀ:: «አባቴና እናቴ የእኔን ከነዓናዊያን ሚስቶች ሳይቀበሏቸው ቀሩ» «አይወዷቸውም:: ሚስትን ማግባት የነበረብኝ ከቤተሰብ ነበር:: አይ፣ መልካም፣ አሁንም ቢሆን እንኳ ጉዳዩ አልዘገየም!» አለ:: ደስ ወደሚለኝ ቤተሰብ ሐረግ እሄዳለሁ:: አጎቴ እስማኤልን እወደዋለሁ:: እርሱ ይስማማኛል:: ባሕሪያችን አንድ ነው:: ከልጆቹ አንዷን እንዳገባ ይፈቅድልኝ እንደ ሆነ ሄጄ ልጠይቀው:: ቤተሰብ ትሆናለች- በግማሽ ጎንዋ ግብጻዊት ናት፤ ያ ግን ምንም አድኅል ዞሮ ዞሮ ቤተሰብ ናት:: እሺ እንደሚለኝ እርግጠኛ ነኝ::»



ከጥቂት ቀን በኋላ፣ ዔሳው የእስማኤል ልጅ ከሆነችው፣ ከሦስተኛዋ ሚስቱ ጋር ከተፍ አለ:: (እስማኤል ማን እንደ ሆነ ታስታውሳላችሁ አይደል? ይስሐቅ ጡት በሚተውበት በዓል ዕለት ይስሐቅን በማበሳጨቱ አብርሃም ከቤቱ ያባረረው ከአጋር የወለደው ልጁ ነበረ::)

አቤት ጉድ! ምስኪኑ ይስሐቅ! ምስኪኗ ርብቃ! ነገሮች ከመጥፎ ወደ ባሰ መጥፎነት መጥፎነት ሄዱባቸው:: ከድጡ ወደ ማጡ እንደሚባለው::

ርብቃ ያዕቆብ ከቤተሰቦቿ የሆነች ሚስት ይዞ ወደቤቱ የሚመጣበትን ቀን ምን ያህል በጉጉት ትብቃለች። ያቺ ቀን ግን ትመጣ ይሆን?

---

ስያዕቆብ ምን እንደሆነለት ለማወቅ በሚቀጥሉት ተ ከታታይ መጽሐፍት «ያዕቆብ- ተረከኸ ያኸ መንትያ እና ያዕ ቆብ የእግዚአብሔር መስፍን» የሚሉትን ርእሶች አንብቡ።

# ታስታውሳላችሁ?

## ምዕራፍ 1 -- ድርብ ችግር

1. መንታ ልጆች ከመወለዳቸው በፊት እግዚአብሔር ለርብቃ የሰጣት መልእክት ምን ነበር?

2. ከመንትያዎቹ ቀድሞ የተወለደው የትኛው ነበር? በጣም የሚወድደው የትኛው ወላጅ ነበር?

3. ቀጥሎ የተወለደው የትኛው መንትያ ነበር? እርሱን በጣም የሚወድደው የትኛው ወላጅ ነበር?

4. ዔሳው ጥሩ አድርጎ ሊሠራው የሚችለው ምን ነበር? ያዕ ቆብስ?

## ምዕራፍ 2 -- ቄንጆ ወጥ

1. የርብቃ ተንከባካቢ (ነርሷ) ስሟ ማን ነበር?

2. ያዕቆብ የሠራውና ዔሳው የሚወድደው ነገር ምን ነበር?

3. ዔሳው ለያዕቆብ የሸጠለት ምን ነበር?

## ምዕራፍ 3 -- «ፀብ የለም!»

1. ፍልስጤማውያን የውኃ ጉድጓዶቹን ምን ያደርጓቸው ነበር?

2. ይስሐቅ አሽከሮቹን ምን አድርጉ አላቸው?

3. ይስሐቅ ለንጉሥ  አቤሜሌክ ምን ውሸት ነገረው?

## ምዕራፍ 4 -- የውኃ ጉድጓድ! ጉድጓድ! ጉድጓድ!

1. ፍልስጤማውያን ውጣልን ባሉት ጊዜ ይስሐቅ ያደረገው ምን ነበር?

2. በቤርሳቤህ እግዚአብሔር ለይስሐቅ የሰጠው ተስፋ ምን ነበር?

3. በንጉሥ አቤሜልክና በይስሐቅ መካከል ምን ስምምነት ተ ደረገ?

## ምዕራፍ  5 -- እነዚያ ምራቶች!

1. ይስሐቅና ርብቃ በዔሳው ሚስቶች የአዘኑት ለምን ነበር?

2. ይስሐቅ ዔሳው ያዘጋጅለት ዘንድ የጠየቀው ምን ነበር?

3. ይስሐቅ  ለዔሳው እሰጥሃለሁ ያለው ምን ነበር?

## ምዕራፍ 6 -- እናት ትፈልገው የነበረውን አገኘች

1. ርብቃ ያደርግ ዘንድ ለያዕቆብ የነገረችው ምን ነበር?

2. ይስሐቅ ለያዕቆብ የሰጠው ባርኮት ምን ዓይነት ነበር?

3. ይስሐቅ ለዔሳው የሰጠው ባርኮት ምን ዓይነት ነበር?

4.  ዔሳው ያዕቆብን ምን አደርገዋለሁ ብሎ ዛተበት?

## ምዕራፍ 7 -- ነገር ግን ያገኘችውን አጣችው

1. ያዕቆብ ከመሄዱ በፊት ይስሐቅ የሰጠው ምን ዓይነት በ ረከት ነበር?

2. ይስሐቅና ርብቃ ያዕቆብን ወደ አጎቱ ወደ ላባ የሰደዱት ለምን ነበር?

3. ሦስተኛዋን ሚስቱን ለማግኘት ዔሳው የሄደው ወዴት ነበር?